# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 140 ጥር 20 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

## በምግብ ዋስትና ላሳዩት ቁርጠኝነት ዓለምአቀፍ ሽልማት ተበረከተላቸው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በምግብ ዋስትናና በተመጣጠነ የምግብ አቅርቦት ላሳዩት ርዕይ፣ አመራርና ቁርጠኝነት የተባበሩት መንግሥታት የምግብ እና የእርሻ ድርጅት(ፋኦ) የአግሪኮላ ሜዳልያ ሸለማቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) በመድረኩ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር የዓለም ምግብ ድርጅት ያበረከተላቸውን የተከበረ ሜዳሊያ በፍጹም ትህትና መቀበላቸውን አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት አምስት ዓመታት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥና የተመጣጠነ ምግብ ተደራሽነትን እውን ለማድረግ ለሠራችው ሥራ እውቅና በመስጠቱ ደስታ እንደተሰማቸውም ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት ረሃብን ሙሉ በሙሉ ከማጥፋት ባለፈ የምግብ ሉዓላዊነትን በማረጋገጥ ሀገራዊ ብልጽግናን እውን

ጠቅላይ ሚኒስትር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል














# የገበታ ፕሮጀክቶች ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን ትልቅ አቅም ይሆናሉ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ባለፉት ዓመታት «ገበታ ለሸገር»፣ «ገበታ ለሀገር» እና «ገበታ ለትውልድ» የተሰኙ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ወደ ሥራ ማስገባቱ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እንደሚያፋጥን የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ተናገሩ፡፡

የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ አቶ መሐመድ ኢሳ ለኢፕድ እንደገለጹት፣ በ«ገበታ ለሸገር»ፕሮጀክት የተገነቡት የአንድነት እና እንጦጦ ፓርኮች፣ የወዳጅነት አደባባይ ቁጥር አንድ እና ሁለት፣ የሳይንስ ሙዚየም፣ የወንዝ ዳርቻዎችንና የመንገድ አካፋዮችን የማልማትና አረንጓዴ የማልበስ እንዲሁም የዐድዋ መታሰቢያ ሙዚየም ግንባታ ለሥራ ዕድል ፈጠራና ለቱሪዝም እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ ይህ ደግሞ ኢኮኖሚው ላይ ለውጥ እንዲመጣ አስችሏል፡፡

ፕሮጀክቶቹ የተገነቡባቸው ቦታዎች ቆሻሻ መጣያ፣

የገበታ ፕሮጀክቶች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# «ኢትዮጵያ አልሸባብን በመዋጋት ለሱማሌላንድ መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክታለች»

- ሳሙኤል ተፈራ (ዶ/ር)

**ዋቅሹም ፍቃዱ**



አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ አልሸባብን በመዋጋት ለሱማሌላንድ መረጋጋትና ለአካባቢው ሰላም ጉልህ አስተዋጽኦ ማበርከቷን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኤሲያና የአፍሪካ ጥናት ማዕከል ተመራማሪ ዶክተር ሳሙኤል ተፈራ አስታወቁ፡፡

ዶክተር ሳሙኤል በኢትዮጵያና በሱማሌላንድ መካከል የተደረገውን ስምምነት አስመልክቶ ከኢትዮጵያ

«ኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# «ከአውደ ርዕዩ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ብሔራዊ ጥቅም በማስከበር ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ተገንዝበናል»

- የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች

ገጽ 6




# ኢትዮጵያ ለጎረቤቶቿ ስጋት ሳትሆን የልማትና የትብብር ምንጭ መሆኗን በይበልጥ ማሳየት ይገባል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ ለጎረቤት ሀገራት ስጋት ሳትሆን የልማትና የትብብር ምንጭ መሆኗን በይበልጥ ማሳየት ይገባል ሲሉ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ ገለጹ፡፡

አምባሳደር ምስጋኑ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከጎረቤት ሀገራት ጋር በትብብር በመሥራት አብሮ ማደግን መርህ ያደረገ ነው።

ኢትዮጵያ ጎረቤት ሀገራት እንደስጋት እንዲመለከቷት ሳይሆን ለሰላምና ልማት የምትሠራ እና የንግድ አጋር መሆኗን ማስገንዘብ ይገባል ብለዋል፡፡

ለቀጣናው ውህደትና መረጋጋት ኢትዮጵያ ቁልፍ ሀገር መሆኗን ማስገንዘብ እንደሚገባ ገልጸው፤ አዳዲስ ወዳጅ ሀገራትን የማፍራት እና ከቆዩ ወዳጅ ሀገራት ጋር ትብብሩን ማሳደግ ላይ ትኩረት መደረጉን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ አጋርነትን፣ ወዳጅነትንና ትብብር ማስፋፋትን ማዕከል ያደረገ መሆኑን ገልጸው፤ ይህንን ተግባር ለሌሎች ሀገራት ማሳየት አለብን ሲሉ ተናግረዋል፡፡

አዳዲስ ወዳጅ ሀገራትን ለማፍራት እንዲሁም ከአፍሪካና ጎረቤት ሀገራት ጋር ያለውን የሰላምና የልማት ትብብር በመሠረተ ልማት የተሳሰረ ለማድረግ እየተሠራ


አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ

እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ከጎረቤት ሀገራት ጋር በትብብር በመሥራት በጋራ ለመልማትና በመሠረተ ልማት ላይ የተሳሰረ ዲፕሎማሲን ለመገንባት ትኩረት ተደርጓል ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲ ሥርዓቷ የአንዱን ሀገር ተጠቃሚ የሚያደርግ በር ዘግታ ለሌላ ሀገር እና ለእራሷ የምትከፍት አለመሆኗን ተናግረዋል፡፡

በጋራ ለማደግና ተጠቃሚ ለመሆን ተጨማሪ የትብብር መስኮችን ለማምጣት የምትሠራ ሀገር መሆኗን ገልጸው፤ በዲጂታል ዲፕሎማሲ ኢትዮጵያን በማስተዋወቅ ብሔራዊ ጥቅምን የሚያስከብሩና መልካም ገጽታን የሚገነቡ ተግባራት ከሁሉም ዜጋ ይጠበቃል ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያን ልማትና ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ይበልጥ ማስተዋወቅ ይገባል ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ ለጎረቤቶቻችን ሰላምና ልማት የምንሠራ መሆናችንን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ሊያሳውቁ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

ከለውጡ በኋላ የዲፕሎማሲ ትብብሩ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ትኩረት ማድረጉን ጠቁመው፤ ግንኙነቱ በአንድ ቦታ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከበርካታ ሀገራት ጋር ትብብሮችን የማስፋፋት መርህ ያደረገ መሆኑን አስታውቀዋል፡፡

ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነትና ትብብር ሲጠናከር ኢትዮጵያን በቀጥታ የሚጠቅም በመሆኑ በትብብር፣ በሰላም፣ በአንድነትና በጋራ ለመልማትና ለመበልጸግ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

ኢትዮጵያ የመልማት ዕድልና የገበያ አማራጭ ያላት ሀገር መሆኗን ለሌሎች ሀገራት በማሳየት ተመራጭ እንድትሆን ማድረግ እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

አዳዲስ ግንኙነቶችን የመመስረትና የሁለትዮሽ ግንኙነቶችን የማጠናከር ሥራ ላይ ትኩረት ተደርጎ እየተሠራ መሆኑንም ጨምረው ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያ በርካታ የዲፕሎማሲ ስኬቶችን እያስመዘገበች ነው ያሉት አምባሳደር ምስጋኑ፤ ብሪክስን መቀላቀልዋ አንዱና ትልቁ የዲፕሎማሲ ስኬት መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡



# ሕገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለመቆጣጠር በትኩረት እየተሠራ ነው

## - ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን ተችሏል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ሕገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለመቆጣጠርና ለመከላከል በትኩረት እየተሠራ መሆኑን የንግድና ቀጣናዊ ትሥሥር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ሊታጣ የነበረ ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን መቻሉም ተገልጿል፡፡

በሚኒስቴሩ የኮሚኒኬሽን ሥራ አስፈጻሚ በላይነሽ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ሕገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለመቆጣጠርና ለመከላከል ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በትኩረት እየተሠራ ይገኛል፡፡

ሕገ ወጥ የቁም እንስሳት ንግድ በስፋት ከሚስተዋልባቸው አካባቢዎች አፋር ክልል ተጠቃሽ መሆኑን ገልጸው፣ በአካባቢው የሚሌ ኳራንታይን በማዘጋጀት ከሀገር የሚወጡ የቁም እንስሳትን በማቆየት ችግሩን መቀነስ ተችሏል ብለዋል፡፡ በዚህም እንደ ሀገር ሊታጣ የነበረ ከስድስት ሚሊዮን ብር በላይ ማዳን መቻሉን ጠቁመዋል፡፡

በእንስሳት ንግድ የተሰማሩ አካላት ሕጋዊ መንገድን እንዲከተሉ ዓለምአቀፍ የቁም እንስሳት ዋጋን በወቅቱ የማሳወቅና ተመጣጣኝ የዋጋ ተመን የማውጣት ሥራ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

በዘርፉ ላይ የሚስተዋሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

እንደ ሥራ አስፈፃሚዋ ገለጻ፤ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ አጋማሽ 130 ሺህ 237 የቁም እንስሳት ለውጭ ገበያ በመላክ 9 ነጥብ 276 ሚሊዮን ዶላር ተገኝቷል፡፡

ለውጭ ገበያ የተላኩት እንስሳትም 127 ሺህ 464 በጎችና ፍየሎች፣ 2 ሺህ 299 ግመሎች እና 474 የዳልጋ ከብቶች መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

የእንስሳቱ መዳረሻም የመን፣ ኦማን፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ሊቢያ እና ሳዑዲ ዐረቢያ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ለውጭ ገበያ ከቀረቡት የቁም እንስሳት 9 ነጥብ 276 ሚሊዮን ዶላር መገኘቱን እና የዕቅዱ 81 ነጥብ 2 በመቶ መፈጸሙን አመላክተዋል፡፡

ለገቢው ማደግ በሕገ ወጥ መንገድ ወደ ውጭ ይወጡ የነበሩ የቁም እንስሳት ወደ ሕጋዊ ሥርዓት እየተመለሱ በመሆናቸው ነው ብለዋል፡፡

አፈጻጸሙ ካለፈው ዓመት ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነጻጸር በእንስሳት የ106 ሺህ እንዲሁም በገቢ የ1 ነጥብ 51 ሚሊዮን ዶላር ብልጫ አሳይቷል ገልጸዋል፡፡


አቶ ታገስ ሙሉጌታ

# ኢትዮጵያ የቀጣናውን የንግድና ኢኮኖሚ ትስስር ለማጠናከር ሰፊ ጥረት እያደረገች ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የቀጣናውን የንግድና ኢኮኖሚ ትስስር ለማጠናከር ሰፊ ጥረት እያደረገች ነው ሲሉ በንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የዓለም አቀፍና ቀጣናዊ ንግድ ትስስር መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ታገስ ሙሉጌታ ገለጹ፡፡

አቶ ታገስ ሙሉጌታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና በኢኮኖሚውና በንግድ ይበልጥ የተሳሰረ እንዲሆን አበክራ እየሠራች ይገኛል።

ከጎረቤት ሀገራት ሕዝቦች ጋር ያለው የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ጠናካራ መሆኑን ጠቁመው፤ በሁሉም መንገድ ያሉ ዕድሎችን በመጠቀም ትስስሩን ለማጠናከር እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ከሶማሊያ፣ ከሱዳን፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከጂቡቲና ከኬንያ ጋር በጋራ ለመሥራት የሚያስችል ስምምነት ተደርጓል ያሉት አቶ ታገሰ፤ ኢትዮጵያ ቀጣይነት ባለው መንገድ ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶች በማድረግ በጋራ ለመልማት በሚያስችል መግባባት እየሠራች መሆኑን አንስተዋል።

በቀጣናዊ ትስስር በኩል የምሥራቅና ደቡብ አፍሪካ የነፃ ገበያ ላይ ኤርትራ፣ ሶማሊያ፣ ሱዳን፣ ጂቡቲ፣ ኬንያ እንዲሁም ኢትዮጵያን ጨምሮ 21 ሀገራት አባል መሆናቸውን የገለጹት አቶ ታገስ፤ ይህም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የሚደረገውን ትስስር ለማጠናከር እንደሚያግዝ አስረድተዋል፡፡

ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ፣ በቀጣናዊና በሁለትዮሽ ግንኙነት ከሀገራት ጋር በንግድና በኢኮኖሚ ግንኙነት ስታደርግ መቆየቷን አስታውሰው፤ ከጎረቤት ሀገራት ጋር ያለው ትስስር እንዲጠናከር የሚያስችል ቅንጅታዊ ሥራ ላይ ሰፊ ተሳትፎ እየተደረገ መሆኑን አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የቀጣናውን ትስስር ዛሬ የጀመረችው ሳይሆን ቀደም ብላ ስትሠራበት የቆየችበት ነው ያሉት አቶ ታገሰ፤ በዓለም አቀፍ፣ በቀጣናዊና በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶች አማካኝነት የምታካሂዳቸው ግንኙነቶች የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መቋቋሙን ተከትሎ መጠናከሩን ገልጸዋል፡፡

የአፍሪካ ኅብረት ሲመሰረት ከፖለቲካ ባለፈ የሀገራትን ንግድና ኢኮኖሚ ትስስር በማጠናከሩ ረገድ በርካታ ሥራዎች የተሠሩ ሲሆን ኢትዮጵያም የዚሁ ትስስር አካል ናት ሲሉ ተናግረዋል።

በአፍሪካ ደረጃ ሀገራት የንግድና ኢኮኖሚ ትስስራቸውን ማጠናከር እንዲችሉ በአቡጃ ስምምነት ላይ የተቀመጡ ስትራቴጂዎችን ኢትዮጵያ እየተገበረች መሆኑን ጠቁመዋል።

የአፍሪካ ነፃ ንግድ ቀጣና ስምምነት የሚፈለገውን ውጤት እንዲያመጣ እየተሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ታገስ፤ ኢትዮጵያ የሀገራትን የጋራ ጥቅም ባከበረ መንገድ ሚናዋን እየተወጣች ነው ሲሉ አመላክተዋል።

ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ድርድር ላይ መሆኗን ጠቅሰው፤ በቀጣይ የሚቀሩ ሥራዎችን ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በትኩረት እየሠራች ነው ብለዋል፡፡

እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ትልቅ ደረጃ እንዲደርሱ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ትኩረት አድርጎ እየሠራ መሆኑን አስረድተዋል።



# አምራች ዘርፉ የውጭ ምንዛሬን በማዳኑ ረገድ የላቀ ሚና እየተጫወተ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አምራች ዘርፉ የውጭ ምንዛሬን በማዳኑ ረገድ የላቀ ሚና እየተጫወተ እንደሆነ የአዲስ አበባ የዘርፍ ማኅበራት ምክር አስታወቀ። ምክር ቤቱ የአዋጅ ማሻሻያ እንዲደረግለት ጠይቋል።

የአዲስ አበባ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ጫኔ ቢተው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ምክር ቤቱ የአምራች ዘርፉን ማነቆዎች እንዲፈቱ በማድረግ ምርትን የማሳደግ እና ተኪ ምርቶችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪ የማዳን ሥራ ሠርቷል። የምክር ቤቱ አባላት ከ7 ሺህ በላይ ሲሆኑ አብዛኛዎቹ በአምራች ዘርፉ ላይ የተሰማሩ ናቸው።

ይህም ለዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ የኤክስፖርት መጠንን በማሳደግ እና የሀገር ውስጥ የገበያ ድርሻን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተ ነው ያሉት አቶ ጫኔ፤ ምክር ቤቱ የአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በማምረቻ ቦታ፣ በመሠረተ ልማት፣ በፋይናንስና በአቅም ግንባታ ዙሪያ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች በመንግሥት ምላሽ እንዲያገኙ ያደርጋል ብለዋል።

ዘርፉ በየጊዜው ራሱን ማብቃት የሚችል የሰለጠነ የሰው ኃይል የሚፈልግ ነው ያሉት አቶ ጫኔ፤ የምክር ቤቱ አባላት በተለያዩ ሙያዎች ግልጽ ግንዛቤ እንዲይዙ በማድረግ የዘርፉን ሀገራዊ የኢኮኖሚ ድርሻ ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት ትልቅ ኃላፊነት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

በተያያዘም የአዲስ አበባ የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የአምራቹን መብትና ጥቅም ለማስከበር የአዋጅ ማሻሻያ እንዲደረግለት ለንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር መጠየቁን የገለጹት፤ የምክር ቤቱ ዋና ጸሐፊ አቶ ጫኔ ቢተው፤ የምክር ቤቱ ማቋቋሚያ አዋጅ 341/95 የአምራቹን መብትና ጥቅም የሚያስከብር አዋጅ እንዲሆን ከስያሜ ጀምሮ ለማስቀየር እየተንቀሳቀሰ ነው ብለዋል።

አዲስ አበባ የዘርፍ ማኅበራት ም/ቤት በአዋጅ ቁጥር 341/95 መሠረት በ1997 ዓ.ም የተመሠረተ መሆኑ ይታወቃል ያሉት አቶ ጫኔ፤ ይህ አዋጅ አሁን ካለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ጋር የሚጣጣም ማድረግ ያስፈልጋል። ይህም የአምራቹን መብትና ጥቅም ይበልጥ እንዲከበር ያደርጋል። ለዚህም የምክር ቤቱ አባላት ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

የሚሻሻለው አዋጅ በ10 ክፍለ ከተሞች በ13 ዘርፎች ተደራጅተው እየሠሩ ላሉት የምክር ቤቱ አባላቶቹ ዘርፈ ብዙ የሆኑ አገልግሎቶችን በመስጠት አምራቾች በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ እንዲሳተፉና የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ምርት በማምረት ተወዳዳሪ እንዲሆኑ አባላትን የመደገፍ ሥራ በመሥራት ላይ እንደሚገኝም አቶ ጫኔ ገልፀዋል።

# በደምበል ሐይቅ ዙሪያ በ3 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር ወጪ ሆቴሎችና ሪዞርቶች እየተገነቡ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ባቱ፡- በደምበል ሐይቅ ዙሪያ በሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ ሆቴሎችና ሪዞርቶች እየተገነቡ እንደሆነ የባቱ ከተማ አስተዳደር አስታወቀ።

የባቱ ከተማ ከንቲባ አቶ አህመዲን እስማኤል ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የባቱ ከተማን የቱሪዝም ከተማ ለማድረግ በደምበል ሐይቅ ዙሪያ በርካታ የልማት ሥራዎች ታቅደው ወደ ተግባር ተገብቷል። አሁን ላይ ስድስት ባለሀብቶች በሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ወጪ በደምበል ሐይቅ ዙሪያ ሆቴሎችና ሪዞርቶች እየገነቡ ይገኛሉ።

የባቱ ከተማን የቱሪዝም መዳረሻና ከተማ ለማድረግ የከተማውን ተፈጥሮ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታን፣ የንግድ እንቅስቃሴን ከኀብፒዎች ጋር የማጣመር ሥራ እየተሠራ መሆኑን የጠቀሱት አቶ አህመዲን፤ በዚህም በደምበል ሐይቅ ዙሪያ በርካታ ሆቴሎች እንዲገነቡ ከተማ አስተዳደሩ ባለሀብቶችን እየደገፈ ይገኛል ብለዋል።

ግንባታው ሁለት ምዕራፍ ያለው ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ መጀመሩን ገልፀዋል። ይህም በአንድ ዓመት ውስጥ እንደሚጠናቀቅ አስረድተዋል፡፡ ይህም ፕሮጀክት «ደምበል የቤተሰብ ባሕር ዳርቻ» የተሰኘ ሲሆን ስድስት ባለሀብቶች እያንዳንዳቸው ለግንባታው 600 ሚሊዮን ብር ወጪ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።



እንደ አቶ አህመዲን ገለፃ፤ ከተማ አስተዳደሩ ለስድስቱ ባለሀብቶች የመሥሪያ ቦታ፣ የአካባቢውን ደህንነት የማረጋገጥ እና አስፈላጊውን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። ባለፉት 60 ዓመታት ወደ ከተማዋ 21 ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ መጋበዝ ተችሏል። ነገር ግን ከዚህ ውስጥ ስድስቱ ብቻ ወደ ሥራ መግባት ችለዋል።

ቀሪዎቹ 15 ኢንቨስተሮች በተሰጣቸው ጊዜ ማልማት ባለመቻላቸው የወሰዱት መሬት ለመንግሥት ተመላሽ ተደርጓል ያሉት አቶ አህመዲን፤ ከለውጡ መንግሥት በኋላ ግን በአንድ ዓመት 36 ኢንቨስተሮችን መጋበዝ መቻሉን ጠቅሰዋል። ከ36ቱ ውስጥ 30ዎቹ ኢንቨስትመንቶች የከተማዋን መሠረተ ልማት የሚያሻሽሉ፣ ለከተማዋ ነዋሪዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ እና የከተማዋን የቱሪዝም መዳረሻነት የሚያጠናክሩ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

ከተማ አስተዳደሩ በሐይቅ ዳርቻ ደረጃውን የጠበቀ ሆቴል ለመገንባት የሚፈልጉ ባለሀብቶችን እያወያየና እየደገፈ ነው። ይህም ወደከተማዋ የሚመጣውን የቱሪስት መጠን እንደሚጨምርም ተናግረዋል። ኢንቨስተሮች ወደ ከተማዋ መጥተው በልማት ሥራ እንዲሳተፉ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

# ጤናማ ሥርዓተ ምግብ ለተሻለ ጤና

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ትንታኔ**

ኢትዮጵያ ከሥርዓተ ምግብ ጋር ተያያዥ የሆኑ ችግሮችን ለመቅረፍ ይረዳኛል ያለችውን የምግብ እና ሥርዓተ ምግብ ፖሊሲ ይፋ ካደረገች አራት ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በፈረንጆቹ 2015 ይፋ ባደረገችው የሰቆጣ ስምምነት ደግሞ በ2030 መቀንጨርን ሙሉ በሙሉ ለማጥፋት አቅዳለች፡፡ ነገር ግን፣ ዛሬም በኢትዮጵያ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሆኑ 39 ከመቶ ሕፃናት የመቀንጨር ችግር ተጠቂዎች ናቸው፡፡

የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እ.ኤ.አ በ2020 ባጠናው ጥናት መሠረት 11 ከመቶ ያህሉ ደግሞ ቁመታቸው ከሰውነታቸው ክብደት ጋር ሲነጻጸር የቀጨጨ ወይም ከተገቢው ክብደት በታች ነው፡፡ መቀንጨርም ሆነ መቀጨጭ በውጫዊው አካል ላይ ብቻ የሚታይ ችግር አይደለም፤ የአእምሮ ዕድገትም ላይ ውስንነትን እንደሚያስከትል የጤና ባለሙያዎች ይናገራሉ፡፡

የመቀንጨር ችግር ያለባቸው ሕፃናት በትምህርት አቀባበላቸው ከሌሎች ሕፃናት የዘገዩ፤ በውጤታቸውም ያነሱ ይሆናሉ፡፡ ነገ ጤናማና ምርታማ ዜጋ መሆን የሚችለው ከእናቱ ሆድ ጀምሮ ለአካላዊና አእምሯዊ እድገቱ የሚያስፈልጉትን ንጥረ ነገሮች ማግኘት የቻለ ሕፃን ነው፡፡

ከሥርዓተ ምግብ አንጻር እንደ ሀገር የግንዛቤ ችግር መኖሩን የዘርፉ ምሁራን ይናገራሉ፡፡ ግንዛቤው አለው የሚባለው የማኅበረሰብ ክፍል ደግሞ፣ የመግዛት አቅሙ አነስተኛ መሆን የሚያስፈልገውን ለማግኘት እንደማይችል የሚናገሩም አሉ፡፡

ወይዘሮ ማኅሌት ንጉሴ በራሷ ሥራ የምትተዳደር ሲሆን የ5 እና 9 ዓመት ልጆች እናት ናት፡፡ እርሷ እንዳጫወተችን ልጆቿ በልተዋል ብላ የምታስበው እንጀራ ሲበሉላት ነው። የተለያዩ አትክልቶችን ለእንጀራ ማባያነትን ታዘጋጃለች። የእንስሳት ተዋጽዖችንም በተቻለ መጠን ትጠቀማለች፡፡

የጥራጥሬና ፍራፍሬ ዘሮች ግን ጥቅም እንዳላቸው ብታውቅም ትዝ ብሏት አትገዛም፡፡ የመግዛት አቅሙ የሚያንሳት ባትሆንም ለልጆቼ ያስፈልጋቸዋል የሚለው ሐሳብ ወደ አእምሮዋ አይመጣላትም፤ ከስንት ጊዜ አንዴ ቤቷ የሚገባው የፍራፍሬ ዓይነት ሙዝ ነው፡፡ ሌሎች የፍራፍሬ ዓይነቶችን እኔም አስታውሼ አልገዛም፣ ልጆቼም ትዝ ብሏቸው አይጠይቁኝም ብላለች፡፡

ሌላዋ እናት ወይዘሮ ርብቃ ይታገሱ የሦስት ልጆች እናት ስትሆን፣ ለልጆቼ ምን ብመግባቸው እንደሚጠቀሙ፤ የትኛውን ንጥረ ነገር ከምን ማግኘት እንደሚችሉ ግንዛቤው አለኝ ትላለች፡፡ የማውቀውን ለመተግበር ግን አቅሜ አይፈቅድም ያለችን ወይዘሮ ርብቃ፣ በተለይ የእንስሳት ተዋጽዖና ፍራፍሬዎችን ለልጆቿ ለመመገብ የፍላጎቷን ያህል



ዶ/ር ሰሎሞን አባተ

አቅሟ እንዳልፈቀደላት ትናገራለች፡፡ «አቅሜ የቻለውን ሁሉ አዘጋጃለሁ፣ ልጆቼ ሰውነታቸው ሞላ ሲል ነው ደስ የሚለኝ፣ እንጀራ ላይ ደከም ካሉ ደግሞ በሶ ማጠጣትን እንደ አማራጭ እጠቀማለሁ» ብላናለች፡፡

በግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የምግብና ሥነ ምግብ ተመራማሪ ዶክተር ሰሎሞን አባተ፣ ሥርዓተ ምግብ አንድ ምግብ ከአመራረት ጀምሮ ገበታ ላይ እስኪደርስ ድረስ ያለውን ሂደት ሁሉ የሚመለከት ጉዳይ ነው ይላሉ። እርሳቸው እንዳሉት፣ አንድ ሰው የተመጣጠነ ምግብ አግኝቷል ወይም ጤናማ ሥርዓተ ምግብን ተከትሏል የምንለው ለሰውነት እድገትና ጤና አስፈላጊ የሆኑ ኃይል ሰጪና ገንቢ ንጥረ ነገሮችን የያዙ ምግቦችን መመገብ ሲችል ነው፤ ከዚህ አንጻር እንደ ሀገር ሥርዓተ ምግብን በሚመለከት ግንዛቤ እና አቅርቦት ላይ በርካታ ችግሮች አሉብን ነው ያሉት፡፡

በተለይ በከተማ የሚኖረው ማኅበረሰብ በብዛት ጣዕም ላይ እንጂ ይዘት ላይ የማተኮር ነገሩ ደካማ ነው ይላሉ፡፡ ትንሽ ግንዛቤ አለው የሚባለው ደግሞ ከአቅም ጋር በተያያዘ የዋጋ ንረት ፍራፍሬና አትክልቶችን በሩቁ እንዲሸሻቸው አድርጎታል፡፡ ግንዛቤው ቢኖረውም የአቅም ማነስ የተመጣጠነ ምግብ እንዳያገኝ እያደረገው ይገኛል፡፡

በተጨባጭ ይህ አካባቢ እንዲህ ነው ብሎ ለመናገር ጥናት የሚጠይቅ ቢሆንም፣ በአንጻራዊነት በገጠራማ አካባቢ ያለው ማኅበረሰብ ከከተማው በተሻለ የተሰባጠረ ምግብ የመመገብ ልምዱ አለው ይላሉ፡፡

የሥርዓተ ምግብ ሥራ በአንድ ጊዜ ተሠርቶ የሚያልቅ የአንድ ሰሞን ሥራ አይደለም ያሉት ሰሎሞን (ዶ/ር)፣ እንደ ማኅበረሰብ የበለጸገ ምግብ በበቂ መጠንና ዓይነት የምናገኝበትን ሥርዓት ለመፍጠር በትኩረት መሥራት እንደሚያሻ ያሳስባሉ፡፡

በኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የሥርዓተ ምግብ ከፍተኛ ባለሙያና ተመራማሪ ዶ/ር እንዳለ አማረ፣



ዶ/ር እንዳለ አማረ

በሀገራችን ከሥርዓተ ምግብ ጋር ተያይዞ በርካታ ችግሮች እንዳሉ ይናገራሉ፡፡ እርሳቸው እንዳሉት በሀገራችን ላለው የሕፃናት መቀንጨርና ከተገቢው ክብደት በታች የመሆን ዋነኛው መንስዔ ጤናማ የአመጋገብ ሥርዓት አለመኖር ነው፡፡ በሀገራችን ላለው የሥርዓተ ምግብ ችግር ሀገራችን ያለፈችባቸው አለመረጋጋቶች አንዱና ትልቁ መንስዔ ነው፡፡ እርሳቸው እንዳሉት፣ ይህ ሁኔታ አስፈላጊ ምርት በአግባቡ ተመርቶ ወደ ማዕድ እንዳይቀርብ ተግዳሮት ፈጥሯል፡፡

ዶ/ር እንዳለ እንዳሉት፣ ከስድስት እስከ 23 ወራት የሚሆናቸው ሕፃናት ከእናት ጡት ወተት በተጨማሪ የተመጣጠነ ምግብ እንዲመገቡና የምግብ ስብጥሩ ሰፊ እንዲሆን ቢመከርም፣ ከእነዚህ ሕፃናት መካከል አስፈላጊ የሚባሉትን 8ቱን ንጥረነገሮች የሚያገኙት 8 ከመቶዎቹ ብቻ ናቸው፡፡ ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ሕፃናት 5ቱን የምግብ ዓይነቶች ብቻ የሚያገኙ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ምግቦችን አሰባጥሮ ካለመመገብ ወይም ተመሳሳይ ዓይነት ምግቦች ደጋግሞ የመመገብ ውጤት ነው፡፡ ችግሩ በተለይ ሕፃናት ለተጓዳኝ የጤና ችግሮች እንዲጋለጡ የሚያደርጋቸውም ጭምር ነው፡፡

የሥርዓተ ምግብ ችግር ለውጥ ያልመጣበትና ያልተሻሻለ ጉዳይ ነው ያሉት ተመራማሪው፤ ችግሩ ማኅበረሰብን በተለይ ሕፃናትን ለዘርፈ ብዙ የጤና ችግር የሚዳርግ፣ እንደ ሀገርም ምርታማ ዜጋ ለማፍራት ተግዳሮት በመሆኑ በዘርፉ የሚሠሩ የምርምር ተቋማት፣ የጤና ሚኒስቴር፣ ግብርና ሚኒስቴርና በተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም በኩል ደግሞ ትምህርት ሚኒስቴር ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው መሥራት እንዳለባቸው አሳስበዋል፡፡

የሥርዓተ ምግብ ሥራ ምግብ ማቅረብ ብቻ አይደለም ያሉት ተመራማሪው፣ ምግብን በማሰባጠር ማኅበረሰብ በተለይም ሕፃናት አስፈላጊ ንጥረ ነገሮችን እንዲያገኙ የሚያስችላቸውን ምግብ መመገባቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋልም ብለዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ሀገራዊ ምክክሩ ለወል ትርክት ትንሣኤ ወሳኝ ነው!

አሁን ላይ በሀገራችን ብዙ ያደሩ የቤት ሥራዎች ከመኖራቸው የተነሳ ዘላቂ ሠላም በማስፈን ልማትን በሁለንተናዊ መልኩ ለማስቀጠል የሚደረጉ ጥረቶች በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ስለመሆናቸው ተደጋግሞ የሚነሳ፤ በተጨባጭም የተጀመረውን ሀገራዊ የለውጥ ሂደት ክፉኛ እየጎዳ ስለመሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው ፡፡

ሀገሪቱ ካላት የረጅም ዘመን የሀገረ መንግሥት ታሪክ፤ ከዚያም በላይ በየዘመኑ ካስተናገደቻቸው መንግሥታት ባሕሪ፤ እንዲሁም በየዘመኑ ከነበረው የሰላም እጦት አንጻር፤ ችግሮች መኖራቸው የሚጠበቅ ቢሆንም፤ እንደ ሀገር እያስከፈሉን ያለው አላስፈላጊ ዋጋ ግን ከግምት በላይ እንደሆነ ብዙዎች ይስማማሉ፡፡

አንዳንድ አፍራሽ ኃይሎችም እነዚህን በጊዜያቸው ተሠርተው ያላለቁ የቤት ሥራዎችን የጥፋት አጀንዳቸው ማማሟቂያ በማድረግ፤ አሁን ላይ ሕዝባችን አብዝቶ የሚሻውን፤ ብዙ ዋጋ የከፈለበትን እና እየከፈለበት ያለውን ሠላምና ልማት እውን እንዳይሆን ፤ በከፍተኛ መነቃቃት ለጀመረው ለውጥ ዋነኛዎቹ ፈተናዎች ሆነውበታል፡፡

እነዚህን ችግሮቻችንን ለዘለቄታው ለመፍታት፤ መንግሥት ብሔራዊ ምክክር ኮሚሽን በማቋቋም፤ መላው ሕዝብ አሉ በሚባሉ ችግሮች ዙሪያ በግልጽና በነፃነት ተመካክሮ የራሱን የመፍትሔ ሀሳቦች እንዲያስቀምጥ የጠራ አቅጣጫ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ነው ፡፡

ኮሚሽኑን ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲዋቀር ከማድረግ ጀምሮ፤ ለስኬታማነቱ የሚያስፈልጉ ድጋፎችን በማድረግ እንደ መንግሥት ያለበትን ኃላፊነት ለመወጣት ረጅም ርቀቶችን ተጉዟል፡፡ እስካሁን እያደረጋቸው ያሉ ተጨባጭ ድጋፎችም ለኮሚሽኑ ተልዕኮ ውጤታማነት ትልቅ አቅም ስለመሆናቸው ተደጋግሞ በኮሚሽኑ በኩል እየተነገረ ይገኛል፡፡

ኮሚሽኑም ወደ ሥራ ከገባ ጊዜ ጀምሮ፤ ለችግሮቹ መፍትሔ የማፈላለጉ ተልዕኮ ከዛሬ አልፎ በመጪዎቹ ትውልዶች ዕጣ ፈንታ ላይ የሚኖረውን የማይተካ አስተዋፅዖ በአግባቡ በመረዳት በኃላፊነት መንፈስ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ እስካሁን ባለው ሂደትም ተስፋ ሰጭ ሥራዎችን እያከናወነ ስለመሆኑ የእለት ተእለት ሥራዎቹ ተጨባጭ ማሳያ ናቸው፡፡

በአሁኑ ወቅት ኮሚሽኑ ከአማራና ትግራይ ክልሎች በስተቀር በክልል ደረጃ ምክክር ለማስጀመር የሚያስችለውን የዝግጅት ምዕራፍ/የተሳታፊዎች ልየታ አጠናቋል፤ በውጭ ከሚገኙ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር የተሳካ ውይይት በማድረግም የጋራ መግባባት ላይ ደርሷል ፡፡

ሀገራዊ ምክክሩ የሁሉምን ኢትዮጵያውያን የሃሳብና የአመለካከት ውክልና ያካተተ፤ የሃሳብ ብዝኃነትን በማስተናገድ በኢትዮጵያ ውስጥ ሀገራዊ መግባባትን ማምጣት የሚያስችል ዓላማ ያነገበ መሆኑ፤ ያደሩ የቤት ሥራዎቻችንን እንደ ትውልድ በኃላፊነት መንፈስ ሠርተን ለችግሮቻችን ዘላቂ መፍትሔ ለማስቀመጥ የተሻለ ዕድል ይዞልን መጥቷል፡፡

ይህንን እድል በመጠቀም ችግሮቻችንን ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ/በውይይት ለዘለቄታው ለመፍታት የጀመርነው ጥረት ፤ ድህነትን ታሪክ አድርገን ለማለፍ እንደ ትውልድ የጀመርነውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ትርክት ስኬታማ ለማድረግ ዋነኛ አቅም እንደሚሆን ይታመናል ፡፡

በተለይም አሁን ላይ እንደ ሀገር ፈተና የሆነብንን የልዩነት ትርክቶች እና ትርክቶቹ እንደ ሀገር እያስከፈሉን ያለውን ያልተገባ ዋጋ በማስቀረት፤ የወል ትርክቶቻችን ትንሣኤ አግኝተው የመላው ሕዝባችን የዘመናት መሻት የሆነውን ብልጽግና እውን ለማድረግ የተጀመረውን መነቃቃት ለማስቀጠል ፋይዳውም ከፍያለ ነው ፡፡

ከሁሉም በላይ መጪው ትውልድ ከትናንት ጎታች ጫናዎች ወጥቶ፤ ዛሬዎቹን በተሻለ መንገድ ተገንዝቦ፤ የራሱን ዕጣ ፈንታ በራሱ በመወሰን፤ ከራሱ አልፎ ለሀገሩ ተስፋ የሚሆንበትን መሠረት መጣል የሚያስችል ትልቅ መነቃቃት ነው!

አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፡- epa@press.et

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የቱሪዝም ኢንዱስትሪው በተሻለ መልኩ እንዲያንሰራራ

ዳንኤል ዘነበ

ኢትዮጵያ የዓለም ቱሪስትን ቀልብ ከሚስቡ ሀገራት መካከል አንዷናት፡፡ ከዓለም የትምህርት፣ ሳይንስ እና ባሕል ተቋም (ዩኔስኮ) የቱሪስት ማዕከላት መካከል ስሟ ደጋግሞ የሰፈረው በሚዳሰሱና በማይዳሰሱ ቅርሶቿ ተጠቃሽ የሆነች ሀገር ነች፡፡ በዩኔስኮ የተመዘገቡ የቱሪዝም ሃብቶቿ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ የቱሪስት ፍሰት እንዲጨምር የጎላ ድርሻ ይኖረዋል፡፡

ይሁን እንጂ ኢትዮጵያ የበርካታ ቱሪዝም ሃብቶች ባለቤት ብትሆንም ዘርፉን በሚገባ አልምቶ ተገቢውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም እንዲያመነጭ ከማድረግ አኳያ ሰፊ ክፍተቶች እንዳሉባት ተደጋግሞ ይገለጻል፡፡ ሌሎች ሀገራት ያልታደሉትን ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ፀጋ ብትታደለም፣ የቱሪስት መዳረሻዎቿ በቅርብ ርቀት የሚገኙ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቶች የመጎብኘት እድላቸው እና ኢኮኖሚ የማመንጨት አቅማቸው በሚፈለገው ደረጃ አይደለም፡፡

መረጃዎችን እና ካርታዎችን መሠረት አድርገው በራሳቸው መንገድ መንቀሳቀስ የሚችሉ፤ በሚፈልጉት ቦታ እየሄዱ እና እያረፉ ያለአስጎብኚ መጎብኘት እንዲችሉ የሚያደርግ አሠራርም አልተዘረጋም፡፡ ለሀገር ውስጥም ሆነ ለሀገር ውጪ ጎብኚ ቦታን የሚጠቁም ወይም መዳረሻው ምን ያህል እንደሚያስሄድ ወይም በጉዞ ሄደት ምን ያህል እንደቀረ በየቦታው የሚገልጹ የመንገድ ላይ ምልክቶች የሉንም፡፡ በየቱሪስት መዳረሻዎች በቂ የሚባሉ የእንግዳ ማረፊያዎች ባይኖሩም ያሉትንም የእንግዶችን መሻት በሚሞላ መስተንግዶና አገልግሎት ከማሟላት አንጻር ውስንነት ይታያል ፡፡

ይህን ዘርፉን የሚፈታተነውን ችግር ለመቅረፍ፤ ከባለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ በመንግሥት በኩል ይህን ታሪክ መቀየር የሚያስችሉ እንቅስቃሴዎች መታየት ጀምረዋል፡፡ በኢትዮጵያ የተደረገው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ (Homegrown Economic Reform) ውስጥ ልዩ ትኩረት ከተሰጣቸው አምስቱ የኢኮኖሚ መሠረቶች ውስጥ ቱሪዝም አንዱ ነው፡፡

በዚህ መልኩ ትኩረት በመስጠት ለዘርፉ ፈጣን እድገት ዋስትና የሚሆኑ ሞዴል የመዳረሻ ልማት ፕሮጀክቶች በ "ገበታ ፕሮጀክቶች" ከዚህ ቀደም ተገቢ ትኩረት ያልተሰጣቸው ቦታዎችን በመምረጥ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች የሚያበረታቱ ናቸው ፡፡ ከነዚህ ውስጥ ቀደም ባለው ጊዜ ተገቢ ትኩረት ሳይሰጠው የቆየው የጎርጎራ ፕሮጀክት አንዱ ነው ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የገበታ ለሀገር ፕሮጀክቶች አካል የሆኑት የጨበራ ጩርጩራ ፓርክና የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክቶችም ሌሎች ተጠቃሽ ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ ከሰሞኑ የተመረቀው የወንጪ-ደንዲ ኢኮቱሪዝም ፕሮጀክት በአጭር ጊዜ ውስጥ ትልቅ ሥራ መሥራት እንደሚቻል የተረጋገጠበት ነው፡፡ መንግሥት ለቱሪዝም ዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ስለመሆኑ አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በሀገራችንም ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው የተሰጠው ልዩ ትኩረት ኢትዮጵያ በቱሪዝም ዘርፍ መጻዔ ጊዜዋ ብሩህ መሆኑን አመላካች ነው ፡፡

ከላይ የተመለከትናቸው ሥራዎች ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው እድገት አዲስ አቅም የሚፈጥሩና ተስፋ የሚያሳድሩም ናቸው፡፡ ሀገሪቱ ካላት የተፈጥሮ ፀጋዎች አንጻር ዘርፉ ከዚህም በላይ ሀገራዊ አቅም እንደሚኖረው ይታመናል፡፡ ለዚህ ግን ከሁሉም በላይ የሠላም ጉዳይ ትኩረት የሚሻ ነው ፡፡

የሠላምን ዋጋ በቱሪዝም ኢንዱስትሪው የማይተካ ሚና እንዳለው ይታመናል ፡፡ ከዚህ አንጻር ሀገራችን እየገጠማት ያለው የሠላም እጦት በቱሪዝም ኢንደስትሪው ላይ አሉታዊ ጥላ እያጠላ ያለና ያልተደፈነ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ሽንቁር ሆኖ ይገኛል፡፡ እንደሚታወቀው በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ተከስቶ በነበረው ግጭት ቀጥተኛ ተጎጂ ከነበሩት ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ነው፡፡

ጦርነቱ በውጪ እና በሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴው ላይ ጉልህ ተፅዕኖዎችን ፈጥሯል፡፡ የውጭ ጎብኝዎች ወደሚጎበኙት አካባቢ ከመሄዳቸው በፊት መጀመሪያ የሚያጣሩት የሠላምና የፀጥታን ጉዳይ ነው፡፡ የሠላም ስጋት እንዳለ ከተረዱ መንቀሳቀስ አይፈልጉም፡፡ ይህ የአብዛኛዎቹ ቱሪስቶች ዋና መገለጫ ነው፡፡ "ሠላም ከሌለ ቱሪዝም የለም" የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡

በሰሜኑ ጦርነት ምክንያት የቱሪዝም እንቅስቃሴ ሲቋረጥ በተለይም ሕልውናቸው ሙሉ በሙሉ በቱሪዝም ገቢ ላይ ለተመሰረተ ግለሰቦች እና ከተሞች ከፍተኛ አደጋ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ ቱሪስቶችን በማስተናገድ የሚታወቁት የአክሱም ሐውልት፣ ከወጥ አለት የተፈለፈሉት የላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፣ ሰሜን ተራሮች የችግሩ ሰለባ ሆነዋል ፡፡

ከግሽን ደብረ ከርቤ እስከ ጎንደር አብያተ መንግሥታት፣ ከአልጣሽ ብሔራዊ ፓርክ እስከ ጣና ሐይቅ ገዳማት፣ ከጭስ ዓባይ ፏፏቴ እስከ ሐይቅ እስጢፋኖስ፣ ከጎርጎራ እስከ ጉና፣ ከዓባይ ሰከላ እስከ ሰቆጣ ሰሃላ በርካታ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊ፣ ባሕላዊ እና ሃይማኖታዊ መዳረሻዎች በሠላም እጦት ምክንያት ሳይጎበኙ በመቅረታቸው ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን አጥተናል፡፡

ለሀገሪቱ የቱሪዝም እንቅስቃሴ መሰናክል የነበረው የሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተቋጨ በኋላ በተለይም በትግራይ አካባቢ የነበረው የቱሪዝም እንቅስቃሴ በተወሰነ መልኩ መነቃቃት ተፈጥሮበታል፡፡ ይህም ሆኖ ግን በአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የሚስተዋሉ ግጭቶች በቱሪዝሙ ኢንዱስትሪው ላይ ሌላ ሥጋት መፍጠራቸው አልቀረም፡፡

በርግጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴው ወደ ነበረበት እንዲመለስ በሀገር አቀፍ ደረጃ መንግሥት፣ ቱሪዝም ሚኒስቴር እና የክልሉ ባሕል እና ቱሪዝም ቢሮ ከአጋር አካላት ጋር እየሠሩ ይገኛሉ፡፡ በዚህም አንጻራዊ የሆኑ መሻሻሎች ታይተዋል ፡፡ ለዚህም በቅርቡ በላሊበላ የተከበረውን የገና በዓልን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

በቅዱስ ላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓልና የቤዛ ኩሉ ሥርዓት በደመቀ ሁኔታ ተከብሯል፡፡ በዚህ ሥነሥርዓት ላይ ከ500 ሺህ በላይ የሀገር ውስጥና የውጪ ቱሪስቶች ታድመውበታል፡፡ ይህም አንጻራዊ ሠላም በመኖሩና የማስተዋወቅ ሥራ በመሠራቱ የተገኘ ውጤት ነው፡፡

የቱሪዝም እንቅስቃሴው መሻሻል ከገቢ በላይ ለቅርሶች እና ለቱሪዝም መዳረሻ አካባቢዎች ዋስትና ነው፡፡ በገና የታየው መነቃቃት በጥምቀት በዓል ላይ በተሻለ መልኩ የውጭ ጎብኝዎች ወደ ሀገሪቱ እንዲመጡ አድርጓል የሚል እምነት አለኝ ፡፡

የቱሪዝም ኢንዱስትሪው እንዲያንሰራራ ለማድረግ በሀገሪቱ ዘላቂ እና አስተማማኝ ሠላም ሊኖራት ያስፈልጋል፡፡ የሀገር ዘላቂ ሰላም ለቱሪዝም እንቅስቃሴና ያንን ተከትሎ ለሚፈጠረው ኢኮኖሚዊ ተጠቃሚነት ዋስትና የሚሰጥ በመሆኑ ለሠላማችን መትጋት ለነገ የምንለው ጉዳይ ሊሆን አይገባም፡፡

**" ጥበብ ይናፍቀኛል ፣**
**ተቻችሎ የሚኖር ሕዝብ ያስቀናኛል ፣**
**ድንቁርና ያስፈራኛል ፣**
**ጦርነት ያስጠላኛል"** እንዳለው ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድሕን፤ ዓለም እንደቀደመው ዘመን በእንግዳ ተቀባይነት ያውቀን ዘንድ ሁላችንም ለሠላማችን ዘብ መቆም አለብን፡፡ በውጭ የሚኖሩ እና በሀገር ውስጥ ያሉ ዜጎች ሁሉ የሀገርን ገጽታ መገንባት እና ዘላቂ ሠላምን ማረጋገጥ ላይ መሥራት ይኖርባቸዋል፡፡ በተለያዩ አካባቢዎች የሚንቀሳቀሱ ነፍጥ ያነገቡ ኃይሎችም ለሠላም የቀረቡ አማራጮችን በኃላፊነት መንፈስ ሊጠቀሙበት ይገባል ፡፡

# «ከአውደ ርዕዩ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ብሔራዊ ጥቅም በማስከበር ወሳኝ ድርሻ እንዳለው ተገንዝበናል»

## - የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች

**ልጅዓለም ፍቅሬ**

**አዲስ አበባ፡-** አውደ ርዕዩ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ብሔራዊ ጥቅምን በማስከበር ረገድ ወሳኝ ድርሻ እንዳለው መገንዘብ ችለናል ሲሉ የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት ሠራተኞች ገለጹ።

የተለያዩ የፋይናንስ ተቋማት አመራሮችና ሠራተኞች «ዲፕሎማሲያችን ለብሔራዊ ጥቅማችን» በሚል መሪ ሃሳብ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የፎቶግራፍ አውደ ርዕይ ሰሞኑን ጎብኝተዋል።

በጉብኝቱ ወቅት ከብሔራዊ ኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኩባንያ የመጡት አቶ ኤልያስ ይታገሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አውደ ርዕዩ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው ዘርፍ ያለውን ዕቅም አቅም በአግባቡ ለማሳየት ያግዛል።

የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው የሀገርን ጥቅም በማስከበር ረገድ ሰፊ አቅም ያለውና የበቁ የፋይናንስ ተቋማትን ለመገንባት የሚያግዝ ነው ያሉት አቶ ኤልያስ፤ አውደርዕዩ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ጥሩ ጅማሮዎች ቢኖሩም በቀጣይ በደንብ መሠራት እንዳለበት የሚያሳይ መሆኑን አስረድተዋል።

ዲፕሎማሲው በተለይ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ ያለው ድርሻ ከፍተኛ እንደነበር ያሳያል፤ አውደ ርዕዩ ከጥንት የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ከፍተኛ ትምህርት የሚወሰድበት እንዲሁም ለወደፊት ዲፕሎማሲው አመላካች ነው ብለዋል፡፡



አቶ ዮናስ በላይ

ከአዲስ ኢንተርናሽናል ባንክ የመጣችው ቃልኪዳን ኃይለመስቀል በበኩሏ፤ ከጥንት ጀምሮ እስካሁን ያለውን የዲፕሎማሲ ጉዞ መረዳት በመቻሏ እንዳስደሰታት ገልጻ፤ ኢትዮጵያ የነበራት ዲፕሎማሲ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅሟን ማስከበር የቻለችበት መንገድ አስተማሪ መሆኑን ጠቁማለች፡፡

አውደ ርዕዩ ለወደፊቱም ጠንካራ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ ለመገንባት የሚያስችል ሰፊ ልምድ የቀሰመችበት መሆኑን ተናግራ፤ በዲፕሎማሲው ረገድ የፋይናንስ ዘርፉን ለማዘመን የቴክኖሎጂ ሽግግርና የልምድ ልውውጥ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ መሆኑን አመላክታለች።



አቶ ቀልቤሳ ከራ

ከኢትዮጵያ መድን ድርጅት የመጡት ጎብኚ አቶ ቀልቤሳ ከራ በበኩላቸው፤ ያለፈውን ታሪክ በአንድ ቦታ ተዘጋጅቶ አዲሱ ትውልድ እንዲመለከተው መደረጉ እንደሀገር በየዘርፉ ለማሳካት የታቀደውን ግብ ለማድረስ እንደሚያግዝ ተናግረዋል።

አውደርዕዩ በቀጣይም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብርና አንድነት የሚያጠናክር የዲፕሎማሲ ሥራዎች እንዲሠሩ ያግዛል ብለዋል።

በተለይ የኢኮኖሚ ዲፕሎማሲው አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያበረከቱ በርካታ አካላት መኖራቸውን መገንዘብ አያዳግትም ያሉት ደግሞ ከንብ ኢንሹራንስ ኩባንያ አክሲዮን ማኅበር የመጡት ጎብኚ አቶ ዮናስ በላይ ናቸው፡፡



ቃልኪዳን ኃይለመስቀል

አውደ ርዕዩን በርካታ ሰዎች እንዲጎበኙት በማድረግ በዘርፉ ያለውን የዕውቀት ክፍተትን መሙላትና ሀገርን ይበልጥ የሚጠቅም መሠረት መጣል እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የፋይናንስ ሴክተሩ ለውጭ ባለሀብቶች ክፍት የማድረግ እንቅስቃሴ እንዲሁም የነጻ ገበያ ምስረታ ወደፊት ተጠናክረው መቀጠል ቢችሉ በኢኮኖሚው ዲፕሎማሲ ትልቅ እምርታ ማምጣት የሚቻልበት እንደሆነ አቶ ዮናስ ጠቁመዋል።

# ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ለማድረግ እየሠራ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ በርካታ ያልተነኩ ጥሬ ሀብቶች፣ ተስማሚ የአየር ንብረትና ለሥራ ትጉ የሆነ ወጣት ትውልድ ያላት ሀገር መሆኗንም ተናግረዋል።

እነዚህን ሀብቶች ታሳቢ በማድረግ የታሪክ አውራ የሆነችውን ሀገር ልማት ወደ ፊት ለማራመድ የመደመር ፍልስፍና ወሳኝ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ባለፉት አምስት ዓመታት በሁሉም ዘርፍ የተከናወኑ ተግባራት ለሚቀጥለው ትውልድ መሠረት የሚጥሉ መሆኑንም አንስተዋል።

ከአምስት ዓመት በፊት ይፋ በተደረገው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ግብርና፣ አምራች ኢንዱስትሪ፣ ቱሪዝም፣ ማዕድንና የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለዕድገት መሠረት መሆናቸው መለየቱን ጠቅሰዋል።

እነዚህ አምስት የኢኮኖሚ ምሰሶዎች ያልተነካ እምቅ አቅም ያላቸው መሆናቸውንም በመድረኩ ተናግረዋል።

በተለይም የግብርናው ዘርፍ ምርታማነት በሀገሪቱ ላለው 120 ሚሊዮን ሕዝብ የማይተካ ሚና እንዳለው በመናገር ሌሎቹም ለኢኮኖሚ ዕድገታችን መሳለጥ መዘውር ናቸው ብለዋል።

በግብርናው ዘርፍ በተከናወኑ የማሻሻያ ተግባራት የሚታረስ መሬት ምጣኔን ከ50 በመቶ በላይ ማሳደግ መቻሉንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅሰዋል።

አሁንም ለመታረስ ዝግጁ የሆነ ሰፊ የመሬት ሀብት መኖሩንም ጨምረው ጠቁመዋል።

በግብርናው ዘርፍ ያለንን እምቅ አቅም አሟጠን ለመጠቀም የጀመርነውን ጥረት አጠናክረን ቀጥለናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተለይም ከፍተኛ ዋጋ የሚያስገኙና ለኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ተክሎችን ለማብቀል የጀመርነው ጥረት ተስፋ ሰጪ ነው ብለዋል።

ድርቅን የሚቋቋሙና የውሃ ፍጆታቸው አነስተኛ የሆኑ ሰብሎችን ለማምረት የተጀመረው ሥራ አበረታች መሆኑን ገልጸዋል።

በተለይም የስንዴ፣ የጤፍ፣ የበቆሎና የገብስ ልማት ሥራዎች ውጤታቸው በተጨባጭ እየታየ መሆኑን ገልጸዋል።

በልዩ ትኩረት በመስኖ ልማት የጀመርነው የስንዴ ልማት ለበርካታ አስርት ዓመታት ከውጭ በማስገባት ጥገኛ የሆንበትን ሂደት የለወጠ ነው ሲሉም አክለዋል።

በስንዴ ልማት ላይ የተከተልነው ዘመናዊ የልማት ቴክኖሎጂ ከስንዴ እጥረት በማላቀቅ ከፍተኛ የምርት ዕድገት አስገኝቶልናል በማለትም ስኬቱን ለመድረኩ አጋርተዋል።

ከድህነት ለመውጣት ያለንን የሰው ሀብት በመጠቀም ምርታማነትን ማሳደግ ይጠበቅብናል ሲሉም አጽንኦት ሰጥተው ተናግረዋል።

አምራች የሆነውን የሰው ሀብታችንን ለመጠቀም ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መመደብ አለብን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለዚህ ደግሞ የሚታረስ መሬትን ከማስፋፋት ባለፈ በወተት፣ በስጋ፣ በዶሮ፣ በዓሣና በማር ምርት ላይ በትኩረት እየሠራን እንገኛለን ብለዋል።

እ.ኤ.አ ከ2018 አንስቶ ከስምንት ባላነሱ የኢንቨስትመንት ከባቢ ጉዳዮች ላይ ማሻሻያ መደረጉን በመግለጽ የተቋማት ግንባታና የሕግና መመሪያዎች ማሻሻያዎች የዚሁ አካል መሆናቸውን አስታውቀዋል።

ይህ ተግባር ኢትዮጵያን ለኢንቨስትመንት ተመራጭ አድርጓታልም ሲሉ ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ የገጠሟትን ፈተናዎች በመቋቋም በተረጋጋ ሁኔታ ላይ ቆማ በዕድገት ወደ ፊት እየገሰገሰች መሆኗን በመጠቆም ይህም የልማት ግቧን ለማሳካትና ኢንቨስትመንትን ለመሳብ እንዳስቻላት ገልጸዋል።

በመድረኩ የተገኙ አቅም ያላቸው ባለሀብቶች በሙሉ መተማመን በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጥሪ አቅርበዋል።

በኢትዮጵያ የለውጥ ጉዞ ውስጥ ድጋፍ ያደረጉ የልማት አጋሮች ላደረጉት እገዛም ምስጋና ማቅረባቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

# «ኢትዮጵያ አልሸባብን በመዋጋት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ፣ ኢትዮጵያ ለቀጣናው ሰላምና መረጋጋት ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከተች ትገኛለች፡፡ በተለይ በአካባቢው የሚንቀሳቀሰውን አልሸባብ የተሰኘ ሽብርተኛ ቡድን በመከላከል ረገድ ጉልህ ድርሻ አበርክታለች፡፡

እንደ ዶክተር ሳሙኤል ማብራሪያ፣ ሱማሌላንድ ለዓለም ንግድ ወሳኝ በሆነው አቅጣጫ ላይ ትገኛለች፡፡ በፖለቲካም የአልሸባብ፣ የሑቲ አማጺያንና ሌሎች ሽብርተኞች የሚንቀሳቀሱበት አካባቢ ስለሆነ ለሀገር ደህንነት ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ቀድሞውኑ አልሸባብን በመዋጋት ለሱማሌላንድ ጸጥታ መረጋጋት ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክታለች፡፡

በሌላም በኩል በሱማሌ በኩል የተገኘው የባሕር በር የጦርነትን ሥጋት ከማስወገዱም በተጨማሪ ኢትዮጵያን የባሕር ኃይል ባለቤት ስለሚያደርጋት ትልቅ ዋጋ ያለው ነው ያሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ ከዚህም ጎን ለጎን ኢትዮጵያ የጀመረችው የባሕር ኃይል የማቋቋም ስምምነት ታሪካዊ ነው ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ ባላት የተፈጥሮ ሀብት ኃያል መሆኗ ለብዙዎች ሥጋት ስለሚሆን በጥርጣሬ ይመለከቷታል ያሉት የፖለቲካ ምሁሩ፤ በዚህም የባሕር በር እንዳይኖራት የተለያዩ ሴራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል፡፡

በአንድ ወቅት በርካታ የባሕር በሮች የነበራት ሀገር የባሕር ኃይል ቀርቶ የባሕር በር ጥያቄ ራሱ ሦስት አስርተ ዓመታትን ማስቆጠሩንም አንስተዋል፡፡

አንዳንዶቹ እንደሚሉት ሶማሌላንድ ከሶማሊያ የተገነጠለች ሀገር ሳትሆን ነፃ ሀገር ናት፡፡ ሀገሪቷ እ.ኤ.አ በ1960 ከእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ነፃ ስትወጣ ከ35 በላይ በሆኑ የዓለም ሀገራት እውቅና የተቸረች ብቻ ሳትሆን ዛሬ 20 የዓለም ሀገራት ለፓስፖርቷ እውቅና በመስጠት ለዜጎቿ አስፈላጊውን አገልግሎት እየሰጡ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሶማሌላንድ ነፃ ሀገር መሆኗን የሚያረጋግጡ መስፈርቶች ናቸው ብለዋል፡፡

እስከ በርሊን ኮንፍረንስ ድረስ ከኢትዮጵያ ውጪ ያሉ የሶማሌ ማኅበረሰብ አባላት በዘመናዊ የመንግሥት አመሠራረት እሳቤ መንግሥት ኖሯቸው አያውቁም ያሉት ዶክተር ሳሙኤል፤ ከዚያ በኋላም ጅቡቲ በፈረንሳይ፣ የአሁኗ ሶማሊያ በጣሊያን እንዲሁም የአሁኗ ሱማሌላንድ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ሥር መውደቃቸውን አውስተዋል፡፡

ከሁሉም አስቀድማ በ1960 ነፃነቷን ያወጀችውም የዛሬዋ ሱማሌላንድ ብትሆንም ታላቋን ሶማሊያ ለመመስረት በራሳቸው ፍቃድ ከሶማሊያ ጋር መቀላቀላቸውን አንስተው፤ ያሰቡት ሳይሳካ ሲቀር በ1991 ፍቺ ፈጽመው ከሶማሊያ ጋር መለያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

ሀገሪቷ ከአራት ዓመታት በፊት ከተባበሩት ዓረብ ኢምሬትስ ጋር የባሕር ኃይል ስምምነት መፍጠሯንና በቀጣይም ከአሜሪካ ጋር ተመሳሳይ ስምምነት ለመፍጠር ዝግጅት ላይ መሆኗን ጠቁመው፤ ከኢትዮጵያ ጋርም ቢሆን በብዙ መልኩ በትብብር ስትሠራ መቆየቷን አመልክተዋል፡፡

# የገበታ ፕሮጀክቶች...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ባዶ መሬቶች፣ ገቢ የማያስገኙና የአካባቢውን ውበት የሚቀንሱ እንደነበሩ ያስታወሱት አቶ መሐመድ፤ በስፍራው ፕሮጀክቶቹ መገንባታቸው አሁን ላይ የውጭ ሀገር እንግዶችን ለመቀበልና ቱሪዝምን ለማሳደግ፣ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እንዲሁም ሀገራዊ ገቢን ለመጨመር ማስቻሉን አመልክተዋል፡፡

ፕሮጀክቶቹ ሀገራዊ ሀብትን በተገቢው ቦታ ማዋል እንደሚገባ እንዲሁም ሀገሪቱ ያላትን ሀብት እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደምትችል ያሳየ በመሆኑ ፕሮጀክቶቹ ሀገራዊ እድገትን እያመጡ እንደሚገኙ አስረድተዋል፡፡ በቀጣይ የተጀመሩት ፕሮጀክቶች ሲጠናቀቁ የሀገሪቱ ማክሮ ኢኮኖሚያዊ እድገት ላይ የራሳቸውን አስተዋፅኦ እንደሚያስቀምጡ አመልክተዋል።

የምጣኔ ሀብት መምህርና ተመራማሪ ሞላ አለማየሁ (ዶ/ር) በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ በ«ገበታ ለሀገር»ፕሮጀክት ጎርጎራ፣ ወንጪና ኮይሻ ተጠቃሽ ናቸው። በ «ገበታ ለትውልድ» ፕሮጀክት ደግሞ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስምንት የቱሪዝም መዳረሻ ሥፍራዎች እየተገነቡ ይገኛሉ። የነዚህ ፕሮጀክቶች መገንባት በክልሎች ውስጥ ኢንቨስትመንት እንዲያድግ አስችሏል።

እንደ ዶክተር ሞላ አባባል፤ ሀገራዊ እድገትን ለማምጣት ልማትን ማፋጠን ተገቢ ነው። በልማት ውስጥ ፕሮጀክቶች ወሳኝ ሚና አላቸው። ፕሮጀክቶቹ ከተጠናቀቁ በኋላ ከሚያመጡት ጥቅም በተጨማሪ ኢኮኖሚን ያነቃቃሉ፣ ፈጠራን ያበረታታሉ፣ ማኅበራዊ ደህንነትን ይፈጥራሉ፣ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ሀብቶች እንዲለሙ መንገድ ይከፍታል፡፡

መንግሥት የፕሮጀክቶቹን ዓላማ በተለያዩ አማራጮች ለሕዝብ ማሳወቅ እንዳለበት በመጥቀስ፤ ይህም ሕዝብ ለፕሮጀክቶቹ ድጋፍና ጥበቃ እንዲያደርግ ዕድል እንደሚሰጥ ገልጸዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ፕሮጀክቶች የሀገር ገጽታን የሚገነቡ፣ የቱሪስት መዳረሻ የሚሆኑ፣ የኢንቨስትመንት አማራጮችን የሚፈጥሩና ሀገሪቱ ከሌሎች ሀገር አንፃር ተመራጭ እንድትሆን የሚያደርጉ መሆናቸውን አብራርተዋል።

# ቀጣናዊ ትስስር - ለአርብቶ አደሩ የላቀ ተጠቃሚነት

**ማሕሌት አብዱል**

በቆላማ አካባቢዎች ኑሮውን ያደረገው የኢትዮጵያ አርብቶ አደር የኑሮ መሠረቱ ለሆኑት እንስሳት ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ብርድና ቁሩ፤ ሐሩሩና ፀሐዩ ሳይበግረው ዘወትር ይማስናል።ለራሱ ይሄነው የሚለው ጥሪት ሳይቀረው ከልጆቹ ለማይለያቸው ከብቶቹ፤ በጎቹ፤ ፍየልና ግመሎቹ ሲል ነጋ ጠባ ይኳዛል፤ በየደረሰበት ጎጆውን ይቀልሳል፤ ደግሞ አፍርሶ ይኳዛል።

አልፎ ተርፎም ጎረቤት ሃገራት እየገባ የእንስሳቱን ቀለብ ይፈልጋል፤ የንግድ ልውውጥ ያደርጋል።እንደእሱ በእንስሳት እርባታ ላይ ከተሠማሩ ጎረቤት አርብቶ አደሮች ጋር ወዳጅነት መሥርቶ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ይፈጥራል።አልፎ አልፎም የጥቅም ግጭት እያጋጠመው ለጉዳት ሲዳረግ ይስተዋላል ::

የኢትዮጵያ መንግሥት የአርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት በማጎልበት ረገድ ፖሊሲ ከማውጣት ጀምሮ የተለያዩ የልማት ስትራቴጂዎችን ነድፎ እየሠራ ይገኛል።በተለይም በየሁለት ዓመቱ በሚከበረው የአርብቶ አደሮች ቀን አማካኝነት የማኅበረሰቡ ችግር ጎልቶ እንዲታይ፤ ብሎም የሚፈታበትን አቅጣጫ ለመጠቆም ጥረት አድርጓል፤ በማድረግ ላይ ይገኛል።

ዘንድሮም ለ19ኛ ጊዜ የሚከበረው ይህ በዓል በባሕል፤ በቋንቋና አኗኗር ዘይቤው ከጎረቤት ሀገራት አርብቶ አደሮች ጋር ያለው ማኅበራዊ መስተጋብር ይበልጥ ሊጠናከር በሚችልበት መልኩ እየተከበረ ነው።በበዓሉ ላይም ከሱዳን በስተቀር የሁሉም ምሥራቅ አፍሪካ ሃገራት አርብቶአደር ተወካዮች የታደሙ ሲሆን የየሀገራቸውን የአርብቶ አደሮች ሕይወትና ስለሚከናወኑ የልማት ሥራዎች የሚያሳዩ መሰናዶ ይዘው ቀርበዋል፡፡

የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስትር ዴኤታ እንድሪያስ ጌታ (ዶክተር) ሰሞኑን ከ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ፣ የዘንድሮው የአርብቶ አደሮች በዓል የምሥራቅ አፍሪካ ሃገራትን ባሳተፈ መልኩ እንዲካሄድ የተደረገበት ዓላማና ፋይዳውን ሲያብራሩ፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ሲከበር የቆየውን የአርብቶ አደሮች ቀን በዓል ዘንድሮ በተለየ መልኩ ጎረቤት ሃገራትን በማሳተፍ ማክበር ያስፈለገው ቀጣናዊ ትስስሩን ይበልጥ ለማጠናከር በማለም እንደሆነ አስታውቀዋል፡፡

‹‹አርብቶ አደርነት የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረ-ቀለም›› በሚል መሪ ሃሳብ እየተከበረ የሚገኘው ይኸው በዓል፣ በዋናነት አርብቶ አደርነት የሁሉንም ሀገራት ሕዝቦች የሚያዋሕድና ኅብረቀለም የሚፈጥር መሆኑን ለማሳየት ታሳቢ ተደርጎ መቀረፁን ሚኒስትር ዴኤታው ያስረዳሉ።በበዓሉ የሚታደሙት አርብቶ አደሮች ባሕላዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስራቸውን ከማጠናከር ጎን ለጎን የጋራ በሆኑ እንደ ድርቅ፤ የጎርፍ አደጋ እንዲሁም ኮንትሮባንድ ንግድ የመሰሉ ችግሮችን ለመፍታት እንዲሁም በልማት አማራጮች ላይ ይበልጥ ተቀራርበው እንዲሠሩ ምቹ እድል ይፈጥራል ተብሎ መታመኑን ያመለክታሉ፡፡

በበዓሉ የአፋር አርብቶአደሮች ከጅቡቲ፤ የሱማሌ ክልል አርብቶ አደር ከሱማሌ ላንድና ከሶማሊያ፤ በኦሮሚያና ደቡብ ያሉት ከኬንያ፤ ጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ያሉት ከደቡብ ሱዳን አርብቶ አደሮች ጋር የባሕል፣ የታሪክ፣ የኢኮኖሚና የገበያ ትስስራቸውን ይበልጥ ስለሚያጠናክሩበት መንገድ የሚወያዩበት እድል እንደተፈጠረላቸው ይጠቁማሉ።

የአርብቶ አደር አካባቢዎችን የቱሪዝምና የኢንቨስትመንት አማራጮች ለማሳየት ጥረት እየተደረገ መሆኑን አንስተው፣ ‹‹የቀጣናው አርብቶ አደሮች ልምድና ተሞክሮቻቸውን በመለዋወጥ የንግድ ትስስራቸውን ይበልጥ እንዲያሳልጡ፤ ብሎም ለሚያገጥሟቸው የጋራ ችግሮች በጋራ የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተጠቃሚነታቸውን እንዲያጎለብቱ እየተደረገ ነው›› ይላሉ።

ተክለዮሐንስ ብርሃኑ (ዶ/ር) በኢትዮጵያ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር ምርምርና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር ናቸው። እንደእሳቸው ገለፃ፤ እንደ ሃገር የአርብቶ አደሮች ቀን መከበሩን ለአርብቶ አደሩ እውቅና ከመስጠት፤ በአካባቢው ያሉ የመሠረተ ልማት ችግሮችን ለመፍታትና የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት ከፍ ለማድረግ የማይናቅ አስተዋፅዖ አበርክቷል።በየአካባቢው ያለውን እምቅ የተፈጥሮ ሃብት ለሀገር ኢኮኖሚ እድገት ለመጠቀም አወንታዊ ሚና ተጫውቷል።

ዘንድሮ ደግሞ ከሀገር በላቀ ቀጣናዊ ትስስር እንዲፈጥር ታሳቢ ተደርጎ መከበሩ ፋይዳው ብዙ እንደሆነ ዳይሬክተሩ ይናገራሉ።በተለይም በሁሉም ሃገራት ያለው አርብቶ አደር አካባቢ በመሠረተ ልማት የተጎዳ፤ በልማትም ወደኋላ የቀረ ከመሆኑ አንፃር መድረኩ ስለችግሮቻቸው በመወያየት፤ የመፍትሔ አቅጣጫ እንዲያስቀምጡ የሚያግዝ እንደሆነ ያስረዳሉ።በፖሊሲ ማዕቀፍ ተደግፈውም በጋራ ፕሮጀክቶች ነድፈው የልማት ሥራዎችን እንዲሠሩ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡

መድረኩ በተለይም ሀገራቱ ድርቅን ለመከላከልና ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ታሳቢ አድርገው የሚሠሩ ምርምሮች፤ የቴክኖሎጂ ሽግግሮችንና ልምዶችን እርስበርስ ለመለዋወጥ የሚያግዝ መሆኑን ያነሳሉ።አንዱ ሀገር ከሌላው ተሞክሮ ከመቅሰም ባሻገር በጋራ በሆኑ ችግሮች ላይ በጋራ ምርምርና ጥናት በማድረግ መፍትሔ እንዲያመጡ ያደርጋልም የሚል እምነት አላቸው።


በተደጋጋሚ ድርቅ የሚያጠቃውን የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ሀገራቱ በተናጠል በሚያደርጉት እሳት የማጥፋት ዘመቻ ብቻ ውጤት ሊመጣ አይችልም ያሉት ዳይሬክተሩ፣ የመካከለኛና የረጅም ጊዜያት እቅዶችን በማውጣት በጋራ ሆነው ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት እና የአርብቶ አደሩን ድርቅ የመቋቋም አቅም ማጎልበት እንዲቻል ተቀናጅተው ሊሠሩ ይገባል።ከዚህ በተጨማሪም የየሀገሩቱ ተመራማሪዎችና የግብርና ባለሙያዎች በመተባበር የግጦሽ መሬትና የመኖ አቅርቦትን በማሻሻል እና በመስኖ ልማት ሥራዎች ላይ ትኩረት አድርገው መሥራት አለባቸው ብለዋል።

የእንስሳት ባለሙያዎች ማኅበር ፕሬዚዳንት ዳንኤል ተመስገን(ዶ/ር) ደግሞ እንደሚሉት፤ በመድረኩ የሀገር መሪዎችና የእርዳታ ተቋማትም የሚሳተፉ መሆኑ በአካባቢው ያሉ ችግሮች፤ የኅብረተሰቡ የልማት ጥያቄዎችና ያሉ ምቹ እድሎች በተጨባጭ እንዲገነዘቡ ያደርጋል።ከዚህም ባሻገር የፖሊሲ ትኩረት እንዲያገኝና በቂ የፋይናንስና ቴክኖሎጂ ድጋፍ እንዲያገኙም የላቀ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።በአካባቢው በየራሳቸው መንገድ የሚሠሩ የልማት ድርጅቶችም ተናበው በቅንጅት እንዲሠሩ መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል።

በምሥራቅ አፍሪካ የልማት በይነ-መንግሥታት (ኢጋድ) የቆላማ አካባቢዎችና የእንስሳት ልማት ዳይሬክተር ደረጀ ዋቅጅራ (ዶ/ር)በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የኢጋድ የእንስሳት ልማት ማዕከል በዋናነት በአባል ሀገራቱ ያለውን የእንስሳት ሃብት እንዲሁም በቆላማ አካባቢዎች ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ አልምተው እንዲጠቀሙ ይሠራል።የስምንቱ የኢጋድ ሀገራት 70 በመቶ የሚሆነው መሬት ቆላማ ነው።በእነዚህ አካባቢዎች ደግሞ ሰብል ማምረት የማይቻል በመሆኑ ኅብረተሰቡ የሚተዳደረው በአርብቶ አደርነት ነው።ኢትዮጵያ ከአብዛኞቹ ሀገራት ጋር በአርብቶ አደሮች አማካኝነት ትተሳሰራለች።አርብቶ አደሩ ዝናብና ግጦሽ ፍለጋ ከአንዱ ሀገር ወደ ሌላው በመሄድ ከሌላ ሀገር አርብቶአደር ማኅበረሰብ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ፈጥሯል።

ይህም ከቦታ ቦታ የመኖር ዘይቤ አሉታዊ ጎን እንዳለው ይናገራሉ።‹‹አርብቶ አደሮቹ ከአንዱ ወደ አንዱ ሃገር ሲንቀሳቀሱ የተለያዩ ችግሮች ይፈጠራሉ፤ በዋናነትም የእንስሳት በሽታና ግጭት ተጠቃሽ ነው›› ይላሉ።እያንዳንዱ ሃገር የራሱን በሽታ ካልተቆጣጠረ በሽታው ወደ ሌላ ሀገር ይዛመታል።ግጭቱን መከላከል ካልቻለ ትልቅ ቀውስ ያስከትላል ሲሉ ያስረዳሉ።በመሆኑም ተቋማቸው በዋናነት የእንስሳት በሽታዎችም ሆነ ግጭቶቹ እንዳይስፋፉ በጋራ የመቆጣጠር ሥርዓት እንዲዘረጋ ኃላፊነቱን ወስዶ እያሠራ ስለመሆኑ ያብራራሉ።

በሌላ በኩል በድንበር አካባቢዎች ያለውን ሰፊ የእንስሳት ሃብት ሃገሮች የተሻለ ገበያ እንዲያመቻቹ ጥረት እንደሚያደርግ ይጠቅሳሉ።በተለይም በዓረብ ሃገራት ከፍተኛ የእንስሳት ሃብት ፍላጎት ስላለ በጋራ እንዲነግዱ የሚደረግ መሆኑን ይጠቁማሉ።ከዚሁ ጎን ለጎንም እንደመንገድ ያሉ መሠረተ ልማቶች ሃገራቱ በጋራ ተቀናጅተው እንዲያለሙ በማድረግ ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን፤ ንግዱም እንዲሳለጥ እየተሠራ መሆኑን ያስረዳሉ።



ኤክስፖው እስከ ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም ለጎብኚዎች ክፍት ሆኖ ይቆያል

‹‹እኛ ትኩረት ሰጥተን እየሠራን ያለነው አካባቢውን በመቀየር የማኅበረሰቡን ተጠቃሚነት ማሳደግና ቀጣናውን በልማት ማስተሳሰር ላይ ነው፤ ይህም በአሁኑ ወቅት ትልቅ ተቀባይነት እያገኘ ነው›› የሚሉት ደረጀ(ዶ/ር)፤ ለዚህም ይረዳ ዘንድ ‹‹ሆርንኦፍ አፍሪካ ኢኒሼቲቭ›› የተሰኘ ፕሮግራም በዓለም ባንክ፤ በአፍሪካ ልማት ባንክ፤ በአውሮፓ ኅብረት ድጋፍ ተግባራዊ መደረጉን ነው ያመለከቱት።

የኅብረተሰብ መሪ የሆኑ ሰዎች በመድረኩ መሳተፋቸው፤ የራሳቸውን ብቻ ሳይሆን ወክለው የመጡትንም ማኅበረሰብ የተዛባ አመለካከት ለመቀየር ትልቅ ፋይዳ እንዳላቸው ይጠቅሳሉ።በግጦሽም ሆነ በተለያየ ምክንያት የሚነሱ ግጭቶች በውይይት እንዲፈቱም ያደርጋልም ይላሉ።ተቋማቸው መሰል የሠላምና የውይይት መድረኮች ማጠናከር ሥራን እየሠራ መሆኑን አንስተው፤ ‹‹በኬንያና ኢትዮጵያ ድንበር ባሉ አርብቶአደሮች መካከል ግጭት እንዳይፈጠር የሃገር ሽማግሌዎችን በማወያየት አለመግባባቶች እንዲፈቱ፤ ሕገወጥ ንግድንም በጋራ መከላከል እንዲቻል ጥረት ያደርጋል›› ሲሉ በአብነት ይጠቅሳሉ።በተጨማሪም የውሃ መሠረተ ልማቶችም በቅንጅት በማልማት የሁለቱም ሃገራት አርብቶአደሮች ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ መሆኑን ያብራራሉ፡፡

በቀጣናው ያለው ሰፊ ሃብት ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግም ሆነ አካባቢውን ከድርቅ ነፃ ማድረግ የረጅም ጊዜ ሥራ መሆኑን ደረጀ (ዶ/ር) አስገንዝበዋል።በተለይም የአየር ንብረት ለውጥን መቋቋም የሚችል ማኅበረሰብ ለመፍጠር አርብቶ አደሩን በቴክኖሎጂ፤ በምርምርና በፋይናንስ የመደገፉ ሥራ ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባው መሆኑን ያመለክታሉ።

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ በበኩላቸው፤ የምሥራቅ አፍሪካ ሃገራቱ በበዓሉ ላይ መታደማቸው ትስስራቸው ምን ያህል የጠነከረ መሆኑንና አርብቶአደር አጥር፤ ድንበር የሌለው መሆኑንም በተጨባጭ አመላክቷል የሚል እምነት አላቸው።‹‹ኢትዮጵያ በዚህ ዝምድና ታምናለች፤ ደግሞም የቀጣናው አሰባሳቢ ሃገር እንደመሆኗ ይህንን ትልቅ አካባቢ /ስቴት/ ይዘን የቀጣናችን ትስስር በማጠናከር አብሮ መበልፀግ ነው የምትፈልገው›› ይላሉ፡፡

‹‹ስንደመር ውበት እንጨምራለን፤ ስንደመር ኃይላችን ይበረታል›› የሚሉት አፈጉባኤው፤ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ሀገራት ምንም እንኳን የተለያዩ ማኅበራዊ፤ ባሕላዊ፤ ኢኮኖሚያዊ እና ሥነ- ምሕዳራዊ ባሕሪያት ቢኖራቸውም፤ ሀገራቱ በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ብቻ ሳይሆን በታሪካቸው እና በሥነ-ሕዝባዊ ባሕሪያቸው ያላቸውን የቅርብ ዝምድና አቅም አድርገን ወደ ብልፅግና ፈጥነው መራመድ እንደሚገባቸው ያስገነዝባሉ።

እንደአፈ ጉባኤው ማብራሪያ፤ የአርብቶ አደር አካባቢዎች በተፈጥሮም የሚጋሯቸው በርካታ ሃብቶች አሉ። በዋናነትም ለልማት ምቹ በሆኑ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ሰፊ መሬቶች፣ እጅግ የበለፀጉ ማዕድናት ባለቤቶች ናቸው።ይሁንና አካባቢዎቹ ከዚህ ሀብት ይልቅ ገዝፈው የሚታዩት የከፋ ድርቅ፣ ጎርፍ፣ ስደትና ግጭቶች ናቸው።ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ የሚከሰተው ተደጋጋሚ ድርቅና የምግብ ዋስትና እጦትም የእነዚህ አካባቢዎች መለያ ሆነዋል።

‹‹‘ይህ ለምን ሆነ?’ ብለን መጠየቅ ይኖርብናል›› የሚሉት አቶ ታገሰ፤ ማኅበረሰቡ በተሰጠው ፀጋ መበልፀግ ሲችል በድህነትና ረሀብ የሚሰቃይበትን ምክንያት የየሃገራቱ መንግሥታትና ፖሊሲ አውጪዎች ራሳቸውን ሊፈትሹ ይገባል የሚል እምነት አላቸው።ሀገራቱ ከምንጊዜውም በላይ ቀጣናዊ ትስስራቸውን ማጥበቅ ቀዳሚ ጉዳያቸው አድርገው መንቀሳቀስ እንደሚገባቸውም ነው አስገንዝበዋል።

እንደአፈጉባኤው ማብራሪያ፤ የአፍሪካ ብሎም የቀጣናው አካባቢዎች የሚራቡት፣ የሚጠሙትና የሚሰደዱት ለመበልፀግ የሚችሉበት ሃብት ሳይኖራቸው ቀርቶ አይደለም።ለአብነት እንኳ አርብቶአደሮች ያላቸው ሰፊ የእንስሳት ሃብት የእነርሱን ሕይወት ብቻ ሳይሆን ለሌላውም ሕይወት መቀየር ትልቅ አቅም ይሆናል።ነገር ግን የሚታየው በተቃራኒው መሆኑ ሁሉንም ሀገራት ሊያስቆጭ ይገባል።የቀጣናው የድህነት ታሪክ ወደፊትም እንዳይቀጥል የምሥራቅ አፍሪካ ብሎም የአፍሪካ አርብቶ አደሮችና መንግሥታት ኃላፊነት ነው።

‹‹የባሕልና የደም ትስስራቸውን ወደ ኢኮኖሚ ትስስር ፈጥኖ መቀየር ለነገ የምንለው የቤት ሥራ አይደለም›› የሚሉት አቶ ታገሰ፤ ለዚህም ቀጣናዊ ትስስሩን ማጠናከር አስፈላጊ እንደሆነ የኢትዮጵያ የምንጊዜም እምነት እንደሆነ ይገልጻሉ።ትስስሩን በኢኮኖሚ ገመድ በማጥበቅ የጋራ ተጠቃሚነትን ማስፈንም የሀገሪቱ የምንግዜም ፍላጎትና ጥረት መሆኑንም አስታውቀዋል።‹‹ኢትዮጵያ ምንጊዜም ትስስርን ታስቀድማለች።ሌላው ቀርቶ የምትገነባቸው ግዙፍ ፕሮጀክቶቿ ጎረቤቶቿም እንዲጠቅሙ፣ ከበረከቱም አብረው እንዲቋደሱ የማድረግ የቁርጠኝነቷ ማሳያ ናቸው›› ይላሉ፡፡

በመሆኑም በዚህ ደረጃ የተጀመረው የትስስር መንፈስ ተጠናክሮ አካባቢው የተቸረውን ውድ የተፈጥሮ ስጦታ በጋራ በማልማትና በመጠቀም፣ ከኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ባሻገርም በቀጣናው ሰላምን እያሰፈኑ መጓዝ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ።እንዲህ ያሉ መድረኮች ትልቅ አቅም የሚፈጥሩ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ይህ መድረክ ቀጣይነት እንዲኖረው መሥራት ይገባልም ብለዋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ትምህርት - የአፍሪካ ኅብረት ጉባኤ ልዩ ትኩረት

ግርማ መንግሥቴ

እንደ ማንኛውም ጊዜ፣ ዘንድሮም የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ እዚህ፣ የአህጉሪቱ መዲና በሆነችው አዲስ አበባ ይካሄዳል። በመሆኑም፣ መዲናዋ አዲስ አበባም እንደ ምንጊዜውም እንግዶቿን ለመቀበል፣ ተቀብላም በጥሩ ሁኔታ ለማቆየት፤ አቆይታም በኋላም ለመሸኘት አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ ትገኛለች።

በዚህ በኅብረቱ ጽሕፈት ቤት በሚካሄደው 47ኛው (ከፌብሯሪ 17 - 18) የኅብረቱ ዓመታዊ ጉባኤ ላይ በርካታ የአህጉሪቱ አንገብጋቢ ጉዳዮች ተነስተው፣ ውይይት ተደርጎባቸውና ውሳኔ ተላልፎባቸው ወደ ተግባር ይቀየራሉ ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን፣ ከእነዚህም መሠረታዊና ሕዝባዊ ጉዳዮች መካከል ፊት መሪው ትምህርት እና በትምህርት ዙሪያ የሚገኙ ጉዳዮች መሆናቸው ታውቋል።

የኅብረቱ (African Union) ድረ ገጽን ጨምሮ በርካታ መገናኛ ብዙኃን እንዳሰራጩት የዘንድሮው የአፍሪካ የመሪዎች ጉባኤ ትኩረት ሰጥቶ የሚነጋገረው በቀዳሚነት አፍሪካ ተኮር ትምህርት እና ሥልጠና ላይ ሲሆን፣ የዘንድሮውን ለየት የሚያደርገው በአህጉሪቱ የሚሰጡ ትምህርቶችና ሥልጠናዎች አፍሪካን የሚመጥኑ፣ የአፍሪካን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘቡ፣ ለአፍሪካ ተስማሚ የሆኑና የአፍሪካን ችግሮች ሊፈቱ በሚችሉ መልኩ እንዲሰጡና አፍሪካዊ አስተሳሰብን የተረዳ ትውልድ መፍጠር ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው።

እንደሚታወቀው አህጉረ አፍሪካ ሳይቸግራት የተቸገረች፤ ሳታጣ ያጣች አህጉር ነች። በመሆኑም ይሄው እስከ ዛሬ እዛው ነች። በተለይ ሠላምና ጦርነትን፣ የእርስ በርስ ግጭቶችንና በሠላም አብሮ መኖርን በተመለከተ ዛሬም በጣም በጣም እዛው ነች። ዘመናዊ እውቀትንም ሆነ ቴክኖሎጂን በተመለከተም እንደዛው።

ወደ ትምህርቱ ዓለም ስንመጣ አፍሪካን የምናገኛት በከፍተኛ ደረጃ ተጎድታ ነው። እንደ ዩኔስኮ (በ26/02/2020 ይፋ የተደረገ) ጥናት ከሆነ ከሳሐራ በታች ብቻ ባሉ ሀገራት እድሜያቸው ከ6 እስከ 11 ከሆኑ ልጆች መካከል ከአንድ አምስተኛ (1/5) በላይ የሆኑት የትምህርት ቤት ደጃፍን ያልረገጡ ናቸው። እድሜያቸው ከ12 እስከ 14 ከሆኑት መካከል ከ1/3 በላይ የሆኑትም እንደዛው። በአጠቃላይ አህጉሪቱ እድሜያቸው ከ15 እስከ 17 ከሆኑት መካከል ከ60% በላይ የሆኑት ምንም ዓይነት የትምህርት እድል የማያገኙ ወይም ያላገኙ፤ በአጠቃላይ በቀጣናው 64 ሚሊዮን በላይ (34 ሚሊዮን ልጃገረዶችን ጨምሮ) መማር የሚገባቸው ዜጎች ከትምህርት ውጪ ናቸው (በ2023 በተደረገ ጥናት መሠረት)።

**ችግሩ በዚህ የማይበቃ መሆኑን ጠቅሰን ወደ ተነሳንበት እንመለስ።**

በተለይ የራስን ማንነት መሠረት ባደረገ መልኩ ትውልድን ከመቅረፅና በእውቀትና ክሂሎት ማስታጠቅ ላይ ሲሠራባት የኖረው ሸፍጥ እራስ አስይዞ የሚያስጮህ ነው። በተለይ "እንግሊዝኛ ተናጋሪ" እና "ፈረንሳይኛ ተናጋሪ" ተብላ ለሁለት መከፈሏ፤ የየሀገራቱም ሥርዓተ ትምህርቶች ይሄንን ክፍፍል ተከትለው መቀረፃቸው አህጉሪቱን ዋጋ አስከፍሏት እዚህ ሁሉ ችግር ውስጥ ዘፍቀዋታል።

በተለይ "ፈረንሳይኛ ተናጋሪ" በሚለው ምድብ ስር የተካተቱት ሀገራት ከማንነታቸው የመነቀል ያህል እስኪቆጠር ድረስ ፈረንሳይኛን ሲጋቱ ነው የኖሩት። ሙሉ የሥርዓተ ትምህርቱ ዝግጅት በፈረንሳዮች (ፈረንሳይ በሠለጠኑ አፍሪካውያን) ሲዘጋጅ ነው የኖረው። ይህ ምንን አስከተለ፤ እነ ማሊ እና የመሳሰሉት ፈረንሳይኛን ከብሔራዊ ቋንቋነት የመሰረዝ እርምጃን እንዲወሰድ ከበቂ በላይ ምክንያት ሆኗቸዋል።

በእነዚህ ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሀገራት ውስጥ ብዙ ነገሮች ተበለሻሽተው የኖሩ ሲሆን፣ በተለይ ከትምህርት ጋር፣ በተለይ በተለይ ከእውቀትና ክሂሎት ጋር በተያያዘ ሲፈፀም የነበረው ግፍ ከዚህ በመለስ የሚባል አይደለም። ለእውቅናና ሽልማት ሳይቀር የሚታጩና የሚሸለሙት በፈረንሳይኛ ቋንቋ የፃፉ እንጂ በሀገራቸው ቋንቋ ለሕዝባቸው የደረሱቱ አይደሉም። "ጎሽ" የሚባሉት በፈረንሳይኛ ያቀነቀኑ እንጂ በራሳቸው ቋንቋና ባሕል ያዜሙ ድምፃዊያን አልነበሩም። ታዲያ ከዚህ በላይ ምን በደል አለ፤ ምንስ ግፍ ይኖራል?




ከእነዚህ ሁሉ በደሎች በመነሳት ይመስላል የዘንድሮው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ መሪ ቃል በ21ኛው ክፍለ ዘመን አፍሪካን የመጠነ ትምህርትና ሥልጠና፤ ችግሮችን መቋቋምና ማሸነፍ የሚችል ሥርዓተ ትምህርትን በመገንባት የትምህርትን ተደራሽነት፣ ጥራት፣ አካታችነት፤ እንዲሁም ዘላቂነት እውን ማድረግ መሆኑን "Educating an Africa fit for the 21st century: building resilient education systems for increased access to inclusive, qualitative, lifelong and relevant learning for Africa." በማለት ያስቀመጠው።

የኅብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበሩ ሙሳ ፋቂ "Our theme for the Year 2024 is devoted to pondering over an in-depth reform of education in Africa, with the prospect of training young people endowed with intellectual, scientific and ethical capacities to serve the transformation of our continent to make it a comfortable and productive living space" በማለት እንዳስቀመጡት፤ የዚህ ዓመት የኅብረቱ መሪዎች ጉባኤ መሪ ቃል በአህጉሪቱ ውስጥ ጥልቅ የሆነ የትምህርት ሪፎርም (ለውጥ) ማድረግ ላይ ያተኮረ፤ ይህም ከሥልጠናዎች ጀምሮ ወጣቱን ትውልድ በእውቀት፣ ሳይንሳዊ አስተሳሰብና ሥነምግባር አቅሙን በማጎልበት አህጉሪቱ እያደረገች ያለውን ሽግግር እንዲያግዝ ማድረግ ነው።

እንደ አሁኑ የኅብረቱ ኮሚሽን ሊቀመንበር ሙሳ (Moussa Faki Mahamat) ጠበቅ ያለ ንግግር አፍሪካ እንደ አህጉር ለመቀጠል ያሏት ሀብቶች ሁለት ሲሆኑ፣ እነሱም አንድነት እና ኅብረት (Unity and Solidarity) ናቸው። ያለ እነዚህ ሁለቱ መሠረታውያን አፍሪካ የትም ልትደርስ አትችልም። እንደየወቅቱ ሊቀመንበር አስተያየት አህጉሪቷ ዛሬ ላይ ከገጠሟት ፈታኝ ፈተናዎች ለመውጣት እነዚህ ሁለቱ ለአፍታም ቸልና "ለነገ" ሊባሉ የሚችሉ ጉዳዮች አይደሉም።

ሙሳ 47ኛውን የአፍሪካ ኅብረት የሥራ አስፈጻሚ ምክር ቤት ስብሰባን ሲከፍቱ ባደረጉት ንግግር ላይ በአፅንዖት እንዳስተላለፉት መልእክት ከሆነ፣ በአሁኑ ሰዓት አህጉሪቱ ወደ ተሻለ የእድገትና ብልፅግና እንድትሸጋገር፣ መቻቻል፣ መተባበር፣ በጋራ መልማት፣ የጋራ ሠላምና ፀጥታን ማስፈን፣ የሠለጠነ ዜጋ መፍጠር እና የመሳሰሉት ነባር እሴቶች እጅጉን ያስፈልጓታል። እንደ አህጉር፣ እነዚህን የራስ ማድረግ ካልተቻለ፤ የወጣቱን እምቅ እውቀትና ኃይል መጠቀም ካልተቻለ (#Youthcharter ይጎብኙ) ኅብረቱ የተመሠረተበትን 100ኛ ዓመት (1963) መሠረት አድርጎ ይደረስበታል የተባለው "አጀንዳ 2063" የሚደረስበት አይሆንም።

እንደ ዘንድሮው የኅብረቱ የመወያያ አጀንዳ ቅደም ተከተል ከሆነ ቅድምና የተሰጠው ለትምህርት ሲሆን፤ ይህም፣ በተለይ ይህንን አጀንዳ እና የኅብረቱ መዋቅራዊ ሪፎርም እንዲሳካ ጨምሮ ለወጣቱ ማስተማርና ግልፅ ማድረግ፤ ፓንአፍሪካኒዝምን ጨምሮ ሙሉ ግንዛቤ እንዲኖረው ማስቻል ይገባል።

ኅብረቱ እንደማንኛውም የጉባኤ ዘመን (የኅብረቱ የ2021 መሪ ሃሳብ "የምንፈልገውን አፍሪካን ለመገንባት ሥነ-ጥበባት፣ ባሕል እና ቅርስ ምሰሶዎች ናቸው" የሚል ነበር)፣ ዘንድሮም ከላይ የጠቀስነውን መሪ ሀሳብ ያነገበ ሲሆን፣ ለዚህም አባል ሀገራቱ በጉዳዩ ላይ በሚገባ መክረውና ዘክረው ወደ ተግባር ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል።

**የኢትዮጵያን ተሞክሮ አበርክቶ**

እንደሚታወቀው፣ ከንጉሡ ጊዜ ጀምሮ ኢትዮጵያ ለአጠቃላይ አህጉረ-አፍሪካ ያላሰለሰ ጥረት ስታደርግ እንደ ነበረ በግልፅ የሚታወቅ ነገር ነው። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጥናት ሰነዶችን እንኳን ወደ ኋላ መለስ ብለን ብንፈትሽ ስለ አጠቃላይ አፍሪካ፣ በተለይም ስለ አፍሪካ የትምህርት ሁኔታ በርካታ ጥናቶች ተካሂደው ነው የምናገኘው። ለአፍሪካ ወደ ፊት መራመድ፣ ከተለያዩ ችግሮች መላቀቅ፣ ሠላምና ፀጥታ፣ ወንድማማችነት፤ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብት ወዘተ ሁሉ በብዛት ተጠንቶ በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ ክፍሎች (ቤተ መጽሐፍቶቹን ጨምሮ) ውስጥ ይገኛል። ይህ አህጉር አቀፍ ኢትዮጵያዊ እንቅስቃሴ መሐል ላይ የተቀዛቀዘ ቢመስልም አሁን አሁን መልሶ እያንሰራራ ያለ ስለ መሆኑ ቀጥለን የምንመለከታቸው ማስረጃዎች ማሳያ ናቸው።

በኢፌዴሪ የትምህርት ሚኒስቴር (በፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2021) ተደርጎ የነበረ አንድ ዓውደ ጥናት (Validation Workshop) የሚነግረን ዐቢይ ጉዳይ ቢኖር የዚህኑ ለአፍሪካ ችግሮች መፈታት አፍሪካዊቷ ኢትዮጵያ እያደረገችው ያለው አስተዋፅዖ ሲሆን፣ አንዱም የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራምን እውን ማድረግን የተመለከተው ነው።

ከላይ በጠቀስነው ዓመት በትምህርት ሚኒስቴር ድረ-ገፅ ላይ "የትምህርት ሚኒስቴር በአፍሪካ ደረጃ የሚተገበረውን ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም መመሪያ እየገመገመ ይገኛል፡፡" በሚለው ዘገባ ስር:-

1) በወርክሾፑ ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት የምገባ ፕሮግራም ውጤታማነት ላይ ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት በማድረግ መመሪያው መገምገሙ 2) መድረኩ በሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ መመሪያ ላይ ውይይት በማድረግ ግብዓት ለመሰብሰብ ያቀደ መሆኑ 3) የትምህርት ቤት ምገባ በትምህርት ቤቶች እንዲተገበር መመሪያ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ መገባቱን እና መመሪያውንም ወጥ እና ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑ 4) አጠቃላይ በአፍሪካ ደረጃ የሚተገበረውን ሀገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ መመሪያ ላይ ለተሳታፊዎች ማብራሪያ መስጠቱ 5) የሀገር በቀል የትምህርት ቤት ምገባ መመሪያ ኢትዮጵያን ጨምሮ በ55ቱም የአፍሪካ ሀገራት ወጥነት ባለው መልኩ ለመተግበር የሚያስችል መሆኑ 6) የሀገር በቀል ትምህርት ቤት ምገባ የትምህርትን ተደራሽነትና ጥራት ለማሻሻል የአፍሪካ ሀገራት የትምህርት ሚኒስትሮች ቀጣናዊ መግባባት ላይ መድረሳቸው 7) ይህን በአፍሪካ ደረጃ የሚተገበረውን ሀገር አቀፍ የትምህርት ቤት ምገባ መመሪያ እንዲገመግሙ ከተመረጡ 16 የአፍሪካ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ መሆኗ ተዘርዝሮ ይገኛል።

ከዚህ የምንገነዘባቸው በርካታ ቁም ነገሮች ቢኖሩም በዋናነት ኢትዮጵያ ለአህጉሪቱ ችግሮች መፍትሔዎችን ከማፈላለግ ባሻገር፣ በራሷ ተግብራ አዋጭ ሆኖ ያገኘችውን ሁሉ ለተቀሩት የአህጉሪቱ አባል አገራት ማካፈሉ ላይ ችላ ብላ የማታውቅ መሆኑን ነው።

ኢትዮጵያ ለየአፍሪካ ኅብረት የትምህርት፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ኮሚሽነርነት በእጩነት አቅርባቸው የነበሩት ፕሮፌሰር ሂሩት ወልደማርያም በወቅቱ ባካሄዱት የምረጡኝ ቅስቀሳ (ዘመቻ) ወቅት በአመራር ጥበባቸው ለኅብረቱ የትምህርት፣ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ኮሚሽን እሴት እንደሚጨምሩ እምነታቸውን ሲገልፁ የነበሩት ፕሮፌሰሯ "በአፍሪካ አካታችና ጥራት ያለው ትምህርት ለማዳረስ እሠራለሁ፤ በትምህርት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን እሞላለሁ" ማለታቸውን፤ ዓለም የተለያዩ የአብዮት ደረጃዎችን በማለፍ በአሁኑ ወቅት የቴክኖሎጂ አብዮት ላይ እንደምትገኝ በማስረዳት አፍሪካም እኩል መሄድ እንዳለባት በአፅዕኖት ሲናገሩ የነበረ መሆኑን፤ ለዚህም የትምህርት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ፈጠራ ያላቸውን ፋይዳ በመዘርዘር በአፍሪካውያን ወጣቶች ላይ ትኩረት በማድረግ እንደሚሠሩ ማብራራታቸውን፤ በአፍሪካ አካታችና ጥራት ያለው ትምህርት እውን በማድረግ የአህጉሩን እምቅ የወጣት ሃብት መጠቀም ላይ የመሥራት ከፍተኛ ፍላጎት ያላቸው መሆኑን መግለፃቸውን እዚህ ጋ በመጥቀስ የኢትዮጵያን ለአፍሪካ ችግር አፍሪካዊ መፍትሔ አቋም አጠናክሮ ማሳየት ይቻላል።

በአጠቃላይ፣ የእስከ ዛሬውን በደልና ግፍ ትተን በዛሬይቱ አፍሪካ ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ብንመለከት በትምህርት ብቻም ሳይሆን በብዙ መልኩ ኋላ ቀርነት አለ። ለዚህ ችግር መቀረፍ ደግሞ፣ ማንንም እንደሚያስማማው፣ መፍትሔው እውቀት ነው። የእውቀት መገኛ መንገዱ ደግሞ ትምህርት እንጂ ሌላ አይደለም። ከዚህ አኳያ የአፍሪካ ኅብረት በዘንድሮው የኅብረቱ የመሪዎች ጉባኤ ልዩ ትኩረቱን ትምህርት እና ሥልጠና ላይ በማድረግ ወጣቱን ለማብቃት መወሰኑ፤ የትምህርት ሥርዓቱም ፍፁም አፍሪካዊ መሠረት እንዲኖረውና የ21ኛዋ ክፍለ ዘመን አፍሪካን የመጠነ እንዲሆን ለመሥራት መነሳቱ፤ አባል አገራትም ይህንን ተግባራዊ ያደርጉ ዘንድ ከወዲሁ እያሳሰበ መሆኑ ሊያስመሰግነው ይገባል።

**መልካም የመሪዎች ጉባኤ እንዲሆን እንመኛለን!!!**

ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# “የወንጪ ሐይቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ ምርጥ የቱሪስት መዳረሻ ተብሎ የተሰየመ የሀገር ሀብት ነው”

አቶ ፋካንሰ ገመቹ
የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ



ፎቶ ፡- ሀዲስ አብርሃ

አስቴር ኤልያስ

**መንግሥት ከመቼው ጊዜ በላይ ለቱሪዝም ሴክተሩ ትኩረት ሰጥቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል። ለዚህም ዋና ማሳያ የሚሆኑት በሀገር አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ክልሎች “ገበታ ለሀገር” በሚል መርሕ እየተገነቡም እየተመረቁም ያሉ ፕሮጀክቶችን ናቸው።**

**ከእነዚህ አንዱ በቅርቡ በኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) የተመረቀው እና የገበታ ለሀገር አካል የሆነው የወንጪ ሐይቅን ለአብነት መጥቀስ ይቻላል። አዲስ ዘመንም በኦሮሚያ ክልል በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን የሚገኘውን የወንጪ ሐይቅን አስመልክቶ እና በዞኑ ስላሉ የቱሪዝም መዳረሻዎች ጋር ተያይዞ ያለውን ሁኔታ እንዲገልጹልን ከዞኑ ባሕልና ቱሪዝም ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ፋካንሰ ገመቹ ጋር ያካሔደውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አጠናቅሮ አቅርቧል። መልካም ንባብ።**

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ዋና ዋና የቱሪዝም መዳረሻ ናቸው የሚባሉት መስሕቦች የትኞቹ ናቸው ?**

**አቶ ፋካንሰ፡-** ዞናችን በቱሪዝም የታወቀ ነው። በእርግጥ ቱሪዝም ሲባል ጽንሰ ሐሳቡ ሰፊ ነው። ብዙ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ እንዲሁም ባሕላዊ እና ታሪካዊ፣ ሰው ሠራሽ እና ተፈጥሯዊ የሆኑ የቱሪዝም መስሕቦች አሉን። ከእነዚህ መካከል እንደዞናችን ለየት ብለው የሚታዩ ደግሞ ሦስት ትልልቅ የቱሪዝም መዳረሻዎች ሲኖሩ፣ አንደኛው በቀርሳ ማሌማ በሚባል ወረዳ የሚገኘው አዳዲ ቤተክርስቲያን ነው።

አዳዲ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ቤተክርስቲያን ነው። አሠራሩ በሰሜኑ የአገራችን ክፍል ከሚገኙት ከእነላልይበላ ጋር የሚመሳሰል ሲሆን፣ ዋና ማሳያውም ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ቤተ ክርስቲያን መሆኑ ነው። ከዚህ በተጨማሪ የሚያመሳስላቸው በአንድ ዘመን የተሠሩ መሆናቸው ነው። ቤተ ክርስቲያኑ አስር ክፍሎች 24 መስኮቶች አሉት። ሙሉ በሙሉ የሚሰጠው አገልግሎት የእምነት ነው። እንደ ቱሪዝም መዳረሻ ስናየው ደግሞ ዋና የዞናችን የቱሪስት መዳረሻ ሆኖ እያገለገለ ነው።

ሁለተኛው የቱሪስት መዳረሻ አዋሽ መልካ ቁንጥሬ ሲሆን ይህ ስፍራ በጣም ታዋቂም ነው። የሰው ቅሪት አካል የሚገኝበት የአርኪዮሎጂ ሳይት ነው። ይህ ቦታ እንደአፍሪካም ሲታይ ብቸኛው ክፍት የአፍሪካ ሙዚየም ተብሎ ይጠራል። ስፍራው ሙዚየም እና አራት ቤቶችም አሉት። አራቱም ቤቶች በአካባቢው የአኗኗር ስልት የተሠሩ ናቸው። ከእነዚህ ክፍሎች ውስጥ አንዱ የአፍሪካን ቅድመ የሰው ልጅ ታሪክ መረጃ የሚሰጥ ነው።

በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአፍሪካ ደረጃ ለሚታወቁ አርኪዮሎጂስቶች ሙሉ መረጃ የሚሰጥ የመጀመሪያው ስፍራ ነው። በተጨማሪም የሰው ልጅ ከቅድመታሪኩ በፊት የሚጠቀምበት ከተለያየ ግብዓት የተሠራ ቁስ ያለበት ሲሆን፣ ሌላኛው ክፍል ደግሞ የሰውም የእንስሳትም አጥንት ያለበት ትልቅ ሙዚየም ነው።

ከእነዚህ መዳረሻዎች በተጨማሪ ወቅታዊ የሆኑ ፏፏቴዎች አሉ። ፏፏቴዎቹ መስከረም እና ጥቅምት አካባቢ አወራረዳቸው በጣም አስገራሚ እና ልዩ ውበት ያለው ነው። በጋ ሲገባ ግን በአወራረዳቸው እየቀነሱ የሚሄዱ ናቸው። እነዚህ ፏፏቴዎች በዞናችን አመያ ወረዳ ውስጥ በርከት ብለው ይገኛሉ።

ትንሽ ለየት የሚያደርገው ሌላው የዞናችን የቱሪስት መዳረሻ የሆነውና ብዙ ሥራም ያልተሠራበት በርካታ ዋሻዎች መኖራቸው ነው። ይሁንና በእነዚህ ዋሻዎች ዙሪያ እስካሁን ጥናት በአግባቡ አልተካሔደበትም። ለምሳሌ ከእነዚህ ዋሻዎች አንዱ አራሬ ዋሻ የሚባል ሲሆን፣ አንድ ግለሰብ መፀዳጃ ቤት ሲቆፍር የተገኘ ዋሻ ነው። ይህ ቦታ ቶሌ ወረዳ ውስጥ ባንቱ በምትባል ከተማ አካባቢ የሚገኝ ነው።

ከአዳዲ ማርያም ጋር ተያይዞ በርካታ ዋሻዎች አሉ። ለምሳሌ ቡርቂቱ የሚባል ዋሻ በዚያ ስፍራ ከሚገኙት መካከል ተጠቃሽ ነው። ሌላው ደግሞ ግብዝና የሚባል ዋሻ ነው። በዋሻ በኩል ዞናችን የሚታወቀው ወንጪ ውስጥ በሚገኘው ስላሴ ዋሻ ነው። በጥቅሉ ዞናችን በሰው ሠራሽም ሆነ በተፈጥሮ ዋሻ በዚህ ደረጃ የሚታወቅ ነው።

ሌላው ትክል ድንጋይ ሲሆን፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም ቦታውን ለማጥናት ይመቸው ዘንድ ከልሎትም ነበር። ትክል ድንጋዮቹ በእድገቱ የእድሜ ባለፀጋ የሆኑ ናቸው። የተለያየ ምልክት የተጻፈባቸውና የተለያየ ቅርጽም ያላቸው ናቸው። ይህ ትክል ድንጋይ ያለው በቀድሞው ደቡብ ክልል ሶዶ ዳቺ በምትባል ወረዳ አካባቢ ነው። ሶዶ ዳቺ የሚባለው ስፍራ በቀድሞው ደቡብ ክልል አዋሳኝ የሆነ ቦታ ነው። ከጢያ ከተማ ጋር የሚዋሰን ሲሆን፣ ጢያ ትክል ድንጋይም መገኛው እዛው አዋሳኙ ቦታ ነው። በእኛ ዞን ውስጥም ልክ እንደ ጢያ ትክል ድንጋይ ምልክቱ ያለበት አይነት ትክል ድንጋይ ይገኛል። ለምሳሌ ከምልክቶቹ መካከል ቦራቴ (ትራስ)፣ ጎራዴ ፣ ታቶ እና መሰል ናቸው።

ይሁንና ዋናው ቁም ነገር የትክል ድንጋዮቹ በዞናችን ውስጥ መኖር ብቻ አይደለም፤ ትልቁ እና አሳሳቢው ነገር ጉዳት እየደረሰባቸው መሆኑ ነው። እነዚህ በአርሶ አደሩ ማሳ ውስጥ ያሉ ትክል ድንጋዮች ጉዳት እየደረሰባቸው ነው። ትክል ድንጋዮቹ ማንም በፈለገው ሰዓት ለተለያየ አገልግሎት ሊያውል የሚችል አይነት ሁኔታ ውስጥ ናቸው። እንዲህ አይነቶቹ ብዙ ጥንቃቄ የሚያሻቸው የሀገር ቅርሶች ሲሆኑ፣ በርከት ያለ ጥናት ቢካሔድባቸው ተጨማሪ መረጃና የሚያስገኙም ናቸው።

**አዲስ ዘመን፡- ትክል ድንጋዮቹ በትክክል እየደረሰባቸው ያለው ጉዳት ምንድን ነው? ኃላፊነቱንስ የሚወስደው አካል ማን ነው?**

**አቶ ፈካንሰ፡-** ትክል ድንጋዮቹ ከሚገኙባቸው አንዱ ቶሌ ወረዳ ሃርሙፎሶሌ ቀበሌ ውስጥ ነው። ድንጋዮቹ የተለያየ ቅርጽና ቁመት ያላቸው ናቸው። ይሁንና ትክል ድንጋዮቹ ያሉበት ወይም የተተከሉበት ቦታ የግለሰብ መሬት ነው። ግለሰብ ደግሞ ቦታውን ለእርሻም ለግጦሽም ይፈልገዋል። ወረዳው ደግሞ ባለፉት ሁለት እና ሦስት ዓመት ውስጥ በፀጥታ ሁኔታው ችግር የተነሳ ወደስፍራው ሰው ሔዶ መሥራት አልቻለም።

ብዙ ጊዜ ወደስፍራው ስልክ በመደወል ስለትክል ድንጋዮቹ እከታተላለሁ። ይህንን የማደርገው ኃላፊነት ስላለብኝ ነው። ክትትል የሚያስፈልግበት አንዱ ምክንያት አንዳንዴ አርሶ አደሩ ትክል ድንጋዮቹን ከማሳው ውስጥ በማውጣት ዳር ላይ ሊያስቀምጥ ስለሚችል ነው። እንዲሁም ደግሞ እያረሱ ባለበት ጊዜም ጉዳት እያደረሱበት ነው።

በእርግጥ እስካሁን የተሰበረ የለም፤ ነገር ግን ወደፊት በዚህ አይነት አካሔድ ምን ሊያጋጥም እንደሚችል አይታወቅም። የእኛም ክትትል ከዚህ ስጋት የተነሳ ስለሆነ የምንፈልገው ትኩረት እንዲሰጠው ነው። ነገ አርሶ አደሩ ሊሰብረውና ለተለያየ አገልግሎት ሊያውለው ይችላል። ስለዚህ አርሶ አደሩም ግንዛቤ ሊያገኝ ይገባል። በእርግጥ ቅርስ የሚመዘገብበት የራሱ የሆነ ቅጽ አለው። በዚያ ላይ መዝግበው እና ኃላፊነቱን ሰጥተን ወጥተዋል።

አንዳንዱን ደግሞ እዛው ባለበት አምስት ያህል ቆርቆሮ ዙሪያውን ያጠርንበት አለ። ከዚህ ባሻገር የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በትክል ድንጋይ እንደቱሪዝም መዳረሻ ብቻ ሳይሆን እንደ ምርምር ማዕከልም ሆኖ የሚያገለግል አቅም ያለው ዞን ነው ማለት ይቻላል። ትክል ድንጋዩ በቁጥር ብዙ ነው። ለምሳሌ ቶሌ ወረዳ ውስጥም ሶዶ ደጬ ውስጥ ያለው በርከት ያለ ነው።

ይሁንና የፀጥታ ጉዳይ ሲታይ አሁን ካሉ ዘርፎች ውስጥ በጣም ጥንቃቄ የሚፈልገው ዘርፍ የቱሪዝም ዘርፍ እንደመሆኑ በፀጥታው ጉዳይ ትኩረት ቢሰጠው መልካም ነው። በተለይ የውጭ አገር ቱሪስቶች ፍሰት የቀድሞውን ያህል አይደለም። አልፎ አልፎ ቢመጡም እምብዛም ምቾት አይሰማቸውም። እንደዚያ ባይሆን ኖሮ ዞናችን እንደክልልም ሆነ እንደ ሀገር አቀፍ ታዋቂ የቱሪዝም መዳረሻነቱ በብዙ ተጠቃሚ ይሆናል የሚል እምነት አለኝ።

**አዲስ ዘመን፡- በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)ተመርቆ ወደ ሥራ የገባው የወንጪ ሐይቅ በዞኑ ያለውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በምን ያህል ደረጃ ያሳልጠዋል ተብሎ ይጠበቃል?**

**አቶ ፈካንሰ፡-** የወንጪ ሐይቅ በዓለም አቀፍ ደረጃም እኤአ በ2021 ወርልድ ቤስት ቱሪስት ቪሌጅ ተብሎ የተሰየመ የሀገር ሀብት ነው።

በመሠረተ ልማት በኩል ሲታይ ዋናው የቱሪስት መዳረሻ ሀብቱ መኖሩ ብቻ ሳይሆን ያለንን ሀብት ማስተዋወቅ ሲቻልም ጭምር ነው። ቀደም ሲል ዘርፉ እንደ አነስተኛ እና ተፈላጊ እንዳልሆነ ይታይ ነበር። ዘርፉን እንዲመሩ እድሉ የሚሰጣቸው አመራሮችም የቅጣት ቦታ ያህል አድርገው ይቆጥሩትም እንደነበር ይታወቃል። በአሁኑ ወቅት ግን መንግሥትም ለዘርፉ የሰጠውን ያህል ትኩረት ለማንም አልሰጠም። ሰው ግብርና፣ የበጋና የመስኖ ስንዴ ይበል እንጅ ለቱሪዝም ዘርፉ የተሰጠው ብልጫ ያለው ነው ባይ ነኝ።

ከዚህ አኳያ ኅብረተሰቡ አካባቢም ያለው አመለካከት ይቀየር ዘንድ ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየተሠራ ሲሆን፣ ይህም ሥራ የቱሪስት መዳረሻ የሆኑ አካባቢዎች ላይ የውስጥ ለውስጥ መንገድ በራሱ በኅብረተሰቡ ተነሳሽነት ለመሥራት የሚያስችል ነው። ዋናው ችግር የመሠረተ ልማት ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ መንገድ ዋናው ነው። የምንከተለው ፍልስፍና ማኅበረሰቡን መሠረት ያደረገ ኢኮቱሪዝም ነው። ይህ በአግባቡ ከተሠራ፣ ለወጣቱ የሥራ እድል መፍጠር ከቻለ እና የአካባቢውን ማኅበረሰብ ከጠቀመ፤ ራሱ ሕዝቡ አገልግሎቱን ሲያይ ሀብቱን ወደመጠበቅ እና መንከባከብ ይሔዳል። ያንን ካላደረገ ግን መጎዳቱ አይቀርም።

በእኛ በኩል ወደ 78 የሚሆኑ የቱሪዝም መዳረሻዎች ላይ ማፒንግ አድርገን ከመሬት አስተዳደር ጋር በመሆን የባለቤትነት ወረቀት ወስደናል። ይህ ቀደም ሲል ያልተለመደ ነው። አሁን ማንም የአባቴ፣ ቅድመ አያቴ መሬት ነው ብሎ ማሰብ አይችልም። እኛ በአሁኑ ወቅት የማኅበረሰብ ተሳትፎ ላይ አመያ እና ሰደንሶዶ ወረዳ ላይ በብዙ ሠርተናል።

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# "የወንጪ ሐይቅ በዓለም አቀፍ...

ከ9ኛው ገጽ የዞረ

ከዚህ የተነሳ ወደ 78 የሚሆኑ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች ላይ የባለቤትነት ወረቀት ይዘናል። እንዲህ ሲባል የቱሪዝም ቦታዎችን ብቻ ሳይሆን የተከበሩ የሚባሉ ቦታዎች ጭምር ነው።

ይሁን እና እንደ ወንጪ መሠረተ ልማቱ ተሟልቶለት ባይሆንም በእኛ አቅም መሥራት ያለብንን ነገር ሠርተናል ብዬ ብዙ መናገር አልችልም። የጀመርናቸው ነገሮች ግን አሉ። ነገር ግን ወደ ወረዳ አካባቢ በሚኬድበት ጊዜ ከፀጥታው ችግር የተነሳ የምንቀሳቀሰው አንዳንዴ በእጀባም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በዞኑ ውስጥ ያሉትን የቱሪዝም መዳረሻዎች በአግባቡ ለመስሕብነት ይበቁ ዘንድ ከዞኑ ባሻገር በክልል ደረጃም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ ምን መደረግ አለበት ይላሉ?**

**አቶ ፈካንሰ፡-** የቱሪዝም ባለድርሻ የሚባለው ሁሉም ሴክተርና ግለሰብም ጭምር ነው። ሚዲያም እንዲሁ በባለድርሻ ነው። በእርግጥ ሚዲያው የሚቀረው ነገር ቢኖረውም የራሱን ሥራ እየሠራ ነው። ለዚህ ምክንያቱ እኛ ዞን ያለው የቱሪዝም መዳረሻን ሰው ማወቅ የቻለው ሚዲያውም በሠራው ሥራ እንጂ እኛ እየደወልን ስለነገርን አይደለም።

በመንግሥት በኩል ያለበት ድርሻ ብዬ የምለው ለዘርፉ ትኩረት መስጠት ነው፤ ይህን ደግሞ እያደረገው ይገኛል። መንግሥት ከአምስቱ ምሰሶዎች ውስጥ ቱሪዝም አንዱ ነው ብሎ ሪፎርም ሠርቷል። በእርግጥ ዘርፉ መሠረተ ልማት እንደ ውሃ እና መንገድ ያስፈልገዋል። ይህ ደግሞ የሚሠራው በመንግሥት እንጂ በኅብረተሰብ አይደለም፤ ኅብረተሰቡ ደግሞ በተለይ ድርሻው የሆነው አካባቢውን ጠብቆ ሠላማዊ በማድረጉ በኩል መሥራት ይጠበቅበታል።

ለምሳሌ በቅርቡ ለምረቃ የበቃው የወንጪ አካባቢ አካባቢውን ጠብቆ ለዚህ ያበቃ ኅብረተሰብ በመሆኑ ሊበረታታ ይገባል። አካባቢውን መንጥሮ ለግብርና ሥራ ለማዋል ባለመነሳሳቱም ሊመሰገን ይገባል፡፡ አካባቢውን ጠብቆ ለዚህ አይነት መስሕብ እንዲበቃ ማድረግ ችሏልና። ኅብረተሰቡ አገር በቀል የሆኑ ትልልቅ ዛፎችን "ለከሰል ይጠቅመኛል" ብሎ አክስሎ ሽጦ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ወንጪን በዚህ አይነት ሁኔታ ላናገኛት እንችል ነበር።

አንዳንድ ቦታ ግን አካባቢያቸውን ያለእውቀት የሚያጠፉና ያጠፉ አሉ። እነርሱ ያንን ያደረጉት በእውቀት እጥረት የተነሳ ሊሆን ስለሚችል ኅብረተሰቡን መውቀስ ከባድ ነው። ሕዝቡ ዛሬ አደራጅተነው የዚህን አካባቢ መንገድ ማውጣት አለብህ ብንለው ያለምንም ማቅማማት ያንን የሚፈጽም ነው። በዚህ ምንም ችግር የለበትም። ስለዚህ ለሕዝቡ በመጀመሪያ መረዳት እንዲኖረው ግንዛቤ መስጠት ነው፡፡ በእርግጥ አንዳንድ ቦታ በተለይም እንደወንጪ አይነት ቦታዎችን ላይ ለጉብኝት የሚመጡ ፈረንጆችን እያዩ ስላደጉ የቱሪዝም ግንዛቤው ይኖራቸዋል። በዞናችን ወደሌላ ወረዳ ላይ ያለው መዳረሻ ላይ ግን የቱሪዝም ጽንሰ ሐሳቡን በራሱ አያውቁምና ግንዛቤው ሊፈጠርላቸው የሚገባ ነው።

ከዚህ ቀደም እኔ በዘርፉ ኤክስፐርት ሆኜ በሠራሁባቸው ጊዜያት ለዘርፉ የነበረው ተቀባይነት ያን ያህል ነበር። በዘርፉ አመራር የነበሩትም የተገባቸውን ያህል አልሠሩበትም። ነገር ግን ዘርፉ ብዙ የሚስብና የሚሠራ ነገር ያለው መሆኑ የሚታወቅ ነው።

ቱሪዝም ጭስ አልባ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ስለመሆኑ ብዙ ተብሎለታል። ስለሆነም በኢኮኖሚ ውስጥ የራሱ የሆነ ድርሻ ይኖረዋል። ከዚህ ጎን ለጎን የሥራ ዕድልም ይፈጥራል። በሌሎች ሀገራት ቱሪዝምን እንደ ሀብት ቆጥሮ ለ24 ሰዓት ሲያስተዋውቀው ይታያል። በእኛ ሚዲያ ግን ምን የመሳሰለ የቱሪዝም ሀብት ሀገራችን እያላት በአግባቡ ማስተዋወቅ ሲገባው ምናልባት ከቱሪዝም መዳረሻዎች መካከል ለዜና መዳረሻ ይሆን ዘንድ ብልጭ ከማድረግ የዘለለ ነገር እምብዛም አይታይም። ጥልቅ የሆነ የማስተዋወቅ ሥራ ላይ ገና ብዙ መሥራት ይቀረናል የሚል አስተያየት አለኝ። በየሚዲያው ትኩረት ተሰጥቶበት ቢተዋወቅ ባለሃብትም በዘርፉ ልማት ላይ ይሰማራል።



**አዲስ ዘመን፡- የወንጪ ሐይቅ በቅርቡ ተመርቆ ሥራ መጀመሩ ይታወቃል፤ ባለፉት ሁለት ሳምንታት ምን አይነት የቱሪስት ፍሰት ነበረው?**

**አቶ ፈካንሰ፡-** አንድ ትልቅ ችግር ነው የሚባለው ከቱሪስት የተገኘውን ገቢ እንዴት ነው የሚለካው የሚለውን ስናይ አንዳንድ ቱሪስት ሀገራችን ኢትዮጵያ መጥቶ ገብተው እስከተመለሱበት ድረስ ያለው ምን ይመስላል የሚለውን ለመለየት እንደ ሀገር አቀፍ ወጥ የሆነ ስሌት የለም። አንድ የውጭ አገር ዜጋ ሀገር ውስጥ መጥቶ አንድ ቦታ ደርሶ ለመመለስ የሚያወጣው ገንዘብ ይኖራል። እንደ ሀገር ግን ከአየር መንገዳችን ጀምሮ መዳረሻው ቦታ ደርሶ ተመልሶ ደግሞ ሒልተን ወይም ኢሊሌ ሆቴል አርፎ ሲሄድ የገንዘብ ዝውውሩ የሚለካው በዚህ ሁሉ ውስጥ ነው። ለቱሪዝም ብቻ ብሎ ይዞ የመጣውን ገንዘብ የሚገመተው በእኛ ገበያ ውስጥ የተዘዋወረው ስንት ነው? ተብሎ ነው።

እኛ ዘንድ ያለው ቁጥር አይተን የማናውቀው ነው ማለት ብር ገቢ ነው። ወንጪ ከተመረቀ ጀምሮ ከ20 ሺ 500 ከሚሆነው የሀገር ውስጥ ጎብኚ ከአራት ሚሊዮን ብር በላይ ሰብስበናል። ወንጪን በሚመለከት የሳምንቱ መዳረሻ ቅዳሜ እና እሑድ ላይ መግቢያ ላይ ብቻ ከ200 ሺ እስከ 500 ሺ እያስገባ ይገኛል። አንድ ጎብኚ ወደ ውስጥ ገብቶ ደግሞ ፈረሱን፣ መርከቡን በመጠቀም ሲዝናና ሌላ ገቢ ይሆናል። ይህ ወንጪ ከመመረቁ ሁለት ሳምንት አስቀድሞ የነበረ ገቢ ነው። ከተመረቀ በኋላ ደግሞ የዚህን አምስት ስድስት እጥፍ ይሆናል ብለን እናምናለን።

አዋሽ መልካ ቁንጥሬን በተመለከተ ባለፈው እኛ ከዩኔስኮ ኤክስፐርቶች ጋር ነበርን። ስለ መልካ ቁንጥሬ የተደራጀ መረጃ ሰጥተናቸዋል። እሱን አይተው ለጉዳዩ እውቅና ለመስጠት ነው የመጡት።

> **ወንጪን እንደ ዞን መግለጽ ማለት ወንጪን ማሳነስ እንዳይሆንብኝ እሰጋለሁና እንደ ሀገር ትልቅ የቱሪዝም መዳረሻ ነው። ከዚህ ቀደም ወንጪ የአፍሪካ ሲውዘርላንድ ብለን የምንጠራት አካባቢ ናት። አንዳንዶች ደግሞ በተለያየ የማኅበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ኢስታንቡል ይሏታል**

አዋሽ መልካ ቁንጥሬ በዩኔስኮ የመመዝገቡ ሁኔታ በቅርቡ ለሀገራችን ሰበር ብሥራት ይሆናል ብለን እናስባለን። ከዚህ ባሻገር ወደአዳዲ ማርያም የውጭ አገር ጎብኚዎች በብዛት መጥተው የሚጎበኙት አንዱ መዳረሻችን ነው። የሀገር ውስጡን ቱሪስት ከተመለከትን ደግሞ ኅዳር 25 ቀን የሚመጣው ብቻ ቁጥሩ በርካታ ስለሆነ አይታወቅም።

በእርግጥ እኛ በሀገር ውስጥ ጎብኚ ምንም ችግር የለብንም። በሳምንቱ መጨረሻ ቀርቶ በአዘቦቱ ቀን መተላለፊያም የለውም። መንግሥት በወንጪ አካባቢ የሠራው ሥራ በጣም ላቅ ያለ ነው።

በዞናችን በቅርቡ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመርቆ ሥራ የጀመረው ወንጪ በትንሹ አንድ ሺ 943 የሚሆን የሥራ እድል መፍጠር ችሏል። በአካባቢው ያሉ ወጣቶችን አደራጅተን የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። ሌላው የሥራ ዕድል መፍጠር ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰቡ የአኗኗር ዘይቤ በራሱ እንዲቀየር አድርጓል። ይህንን ማምጣት የቻለው ቱሪዝሙ ነው።

ወንጪን እንደ ዞን መግለጽ ማለት ወንጪን ማሳነስ እንዳይሆንብኝ እሰጋለሁና እንደ ሀገር ትልቅ የቱሪዝም መዳረሻ ነው። ከዚህ ቀደም ወንጪ የአፍሪካ ሲውዘርላንድ ብለን የምንጠራት አካባቢ ናት። አንዳንዶች ደግሞ በተለያየ የማኅበራዊ ትስስር ገጽ ላይ ኢስታንቡል ይሏታል። በእኔ አተያይ ከሁለቱም ዓለም አቀፍ ቦታዎች ወንጪ ይበልጣል። ምናልባትም ሀገራቱ የገንዘብ ችግር ስለሌለባቸው ሰው ሠራሽ ማሳመሪያ አድርገው አሳመሩት እንጂ ልክ እንደ ወንጪ ተፈጥሯዊ ውበት የተላበሰ ቦታ አይደለም። እኛ ደግሞ ተፈጥሮ በዛ መልኩ የለገሰችን ነን። ይሁንና ለአሁኑ ገንዘብ በእጃችን ስለሌለ የዚያን ያህል መዋዕለ ንዋይ ገና አላፈሰስንበትም። በጥቅሉ ግን የወንጪን ውበት አሁን ለመግለጽ በጣም ከባድ ነው። እኔ መንግሥት ለቱሪዝም በዚህ መልኩ ትኩረት በሰጠበት በዚህ ዘመን እዚህ ወንጪ አካባቢ በመገኘቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። በወንጪ አካባቢ ቀንና ማታ ሳንል ስንሠራ የነበረው ለሁለት ዓመት ያህል ነው።

እንደ ዞንም ወጣቶችን ከማደራጀት ይልቅ ወደ 700 ሺ የሚሆን ብር አውጥተን 36 ያህል ሳይክል ገዝተንላቸዋል። ይህን ያደረግነው በአንድ በኩል የሥራ ዕድል በሌላ በኩል ደግሞ ቀጣይነት ያለው ፕሮጀክት ለምሳሌ የቱሉ ቦሎ ቡድን እንደ ኢትዮጵያ ሆነ እንደ አፍሪካም እየተወዳደረ ያለ ቡድን ነው። ከዚህ የወንጪ ደንዲ ባይስክል ቡድን ፕሮጀክት ለማድረግ እየሠራን ነው። በእርግጥ የቤት ሥራችን ከእኛም ከፍ ያለ ነው፤ እኛ የምንሠራው እንዳለ ሆኖ ማለት ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በቀጣይ ወንጪን የት ለማድረስ አቅዳችኋል?**

**አቶ ፈካንሰ፡-** ዞናችንን ኦሮሚያ ላይ ሆነው ሲያስቡ በአንድ በኩል በአዋሳኙ አካባቢ ምክንያት ይቆጠር የነበረው እንደ ደቡብ ነው። የዞኑ የኋላ ታሪክ ጉራጌ እና ጨቦም ነበር። ይህ ዞን በሀገሩ የሚኮራ እና ለሀገራቸው ሲሉ ብዙ መስዋዕትነት የከፈሉ ጀግኖች የፈለቀበት ነው።

በጥቅሉ እኛ አሁን እየሠራን ያለነው ወንጪ ቱሪዝም ሆኖ ቱሪስትን አምጥቷል። ይህ የቱሪዝም ዘርፉ ድርሻ ነው። የባሕሉ ድርሻስ? ባሕሉን ወደኢኮኖሚ እንዴት እንቀይር የሚለውን ገና ነው። ስለዚህ እቅዳችን የኦሮሞ አልባሳትና ባሕላዊ እቃውን እና መገለጫውን የያዘ አንድ ጋለሪ በማቋቋም ያንን ለቱሪስት ማሳየት ነው። ዓመትን ጠብቆ ፌስቲቫል ማዘጋጀትና ወጥቶ መጨፈር ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ ዘርፍ እንዲሆን ባሕላችንን እንዴት መሸጥ አለብን የሚለውን እንደ ፕሮጀክት ወንጪ ላይ ይዘናል። ስለዚህ የወንጪ ፕሮጀክት በሂደት ያደገ የሚሄድ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ አመሰግናለሁ።**

**አቶ ፈካንሰ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## ‹‹ካባ›› - የሙሽሮች መድመቂያ ፤ የክብር መግለጫ ...

**ሰሚራ በርሀ**

‹‹ካባ›› ቀደም ሲል የክብር መገለጫ፣ በንጉሣውያን ቤተሰብ የሚዘወተር፣ የሀብት መገለጫም ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በአብዛኛው ሕዝብ ዘንድ የሚለበስም አይደለም፤ የሚለብሱት ቢኖሩም በየቀኑ የሚለበስ አይደለም።

አሁን አሁን ከባሕላችን አንዱ በሆነው የሠርግ ሥነ-ሥርዓት ወቅት ለመለስ ሙሽሪት እና ሙሽራው በሚለብሱት የሀገር ባሕል ልብስ ላይ ካባ ይደርባሉ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዓተ ጋብቻቸውን የሚፈጽሙ የእምነቱ ተከታዮች ደግሞ የመስቀል ምስል ያረፈበትን ካባ እና ተመሳሳይ የሆነውን በአናት ላይ የሚጠለቅ አክሊል አድርገው የጋብቻ ሥርዓታቸውን ያከናውናሉ።

በተለያዩ ሁነቶች፣ የምስጋና እና የሽልማት ፕሮግራሞች፣ በሥራቸው ከበሬታን ላተረፉ ሰዎች ካባ በሽልማትና የክብር መገለጫነት ይበረከትላቸዋል። በትዳራቸው በርካታ ዓመታትን በአብሮነት ያሳለፉ ጥንዶችም እንዲሁ በትዳር የቆዩበትን የብር፣ የወርቅ እዮቤልዩ በዓል ሲያከብሩ ካባ ይደርባሉ። ረጅም እድሜ ያስቆጠሩ ሰዎች የልደት በዓላቸውን ለማክበር የሚደርቡትም ነው።

በሌሎች አገራት ኢትዮጵያን ወክለው የሚሠሩ አምባሳደሮችም ሀገራቸውን ያስተዋውቁበታል። ከዚህም ባሻገር ለሌላ ሀገር ዜጋ እና ለኢትዮጵያ በጎ ነገር ላበረከቱ የሥራ ኃላፊዎችም ያላቸውን ክብርና ምስጋና ካባ በመስጠት እና በማልበስ ይገልጻሉ።

ይህ ካባ አሁንም ተወዳጅነቱ እና ተፈላጊነቱ ቀጥሏል። አቶ ዓለምሰገድ አሰፋ የዚህ በጥቂት ሰዎች እጅ ላይ ብቻ የሚገኝ ካባ ሙያ ባለቤት ነው። በዚህ ሥራም ረጅም ዓመታትን አስቆጥሯል። በሚኖርበት አካባቢ ይህንን ሙያ የሚያወቁ ሰዎች በመኖራቸው ወደሥራ ቦታቸው በመሄድ ሙያውን ተምሮ አሁንም ድረስ የገቢ ምንጩ አድርጎት እየሠራ ይገኛል።

በሙያው የ15 ዓመት ልምድ ያለው ዓለምሰገድ፤ የካባ ሥራ ቀላል የማይባል ጊዜ እና ጉልበት እንደሚጠይቅ ይናገራል። ዓለምሰገድ እንደሚለው፤ ቀደም ባሉት ጊዜያት ካባ ሲባል የተለመደው ጥቁር ከፋይ ጨርቅ ላይ ከላይ እስከታች ለየት



ባለመልኩ ወርቃማ በሆነ የክር ቀለም የተጠለፈ ሲለበስም የተለየ ውበትን የሚያጎናጽፍ ነው። ካባ አሁን በተለያዩ የቀለም አማራጮችና ዲዛይኖች እየተሠራ ነው።

በገበያው ላይ እንደ መግባቢያ ‹‹የሙካሽ ካባ›› ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ መነሻውም ካባ ለመሥራት እንደ ግብዓት የሚያገለግለው ‹‹ሙካሽ›› የሚባል ክር በካባው ላይ ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ ነው። ካባ ምንም እንኳን በኛ ሀገር ብቻ የሚታወቅ የክብር ልብስ ቢሆንም፣ ዓለምሰገድ በቆየባቸው የሥራ ዓመታት ካባ ለመሥራት የሚጠቀምባቸው የከፋይ ጨርቅና ሙካሽ ግን ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ከውጭ ሀገር የሚገቡ ናቸው።

‹‹ ዋናው ግብዓት ሙካሽ ሲሆን ሌሎች እቃዎችን ሰዎች ሲያመጡ እግረ መንገዳቸውን እንዲያመጡልን እናደርጋለን›› የሚለው ዓለምሰገድ፤ ቋሚ የሆኑ አስመጪዎች ባለመኖራቸው ካባ ሳይሠሩ የሚቆዩባቸው ጊዜያት መኖራቸውን ይናገራል። ግብዓቱ ከተለያዩ ሀገሮች ይመጣል፤ የህንድ ሙካሽ፣ የግሪክ ሙካሽ እየተባለ ይጠራል። ሕንዳውያን ይህንን ሙካሽ ለጌጣጌጥ መሥሪያነት ይጠቀሙበታል።

አንድ ካባ ተሠርቶ ለደንበኞች ሲቀርብ ለሠርግ ከሆነ ለሙሽሮች አንድ ላይ ጥንድ ካባ ይዘጋጃል። ዓለምሰገድ አንድ ካባ ብቻውን ሠርቶ ለማጠናቀቅ 15 ቀናት እንደሚወስድ ጠቅሶ፣ ካባው በስድስት ባለሙያዎች ከተሠራ ደግሞ አንድ ሳምንት ይወስዳል ።

ካባው ላይ ያሉት ዲዛይኖች ይህ ነው የሚባል ስም እንደሌላቸው የሚያነሳው ዓለምሰገድ፤ ጠላፊው በጊዜ ሂደት እና በሥራ ልምድ ቆይታው የራሱን ፈጠራ በማከል እንደሚሠራው ይገልጻል።

ደንበኞችም ዓይናቸው ያረፈበትን አንዳንዴም ደግሞ ታዋቂ ሰዎች ላይ የተመለከቱትን ዲዛይን እንደሚመርጡ ገልጾ፤ የአሠራር ሂደቱ የሚጀምረው ደንበኞች በመረጡት የከፋይ ቀለም ተለክቶ ከተቆረጠ በኋላ ነው፤ ከዚያም በአቡጀዲ ጨርቅ ላይ ተወጥሮ በስፌት ክሮች ዲዛይን ከወጣለት በኋላ በክሩ በመመራት በሙካሽ ይጠለፋል ሲል ያብራራል።

‹‹አንድ ሰው የካባ ሥራ ለመልመድና በሥራው ባለሙያ ለመባል ዓመታትን ይወስድበታል›› የሚለው ዓለምሰገድ፤ በሙያው ብቁ የሰው ኃይል እጥረት እንዳለ ይናገራል። ለዚህም ምክንያቱ ሙያውን ለመልመድ የሚያስችል ትምህርት ቤት በሀገሪቱ ባለመኖሩም መሆኑን ገልጿል። በሀገራችን በልምድ እየተላለፉ ከመጡ የሙያ ዓይነቶች እንደ ሽመና እና የካባ ሥራን ጨምሮ ሰዎች በፍላጎት ልምድ ካላቸው ባለሙያዎች ተጠግተው የሚማሩበት ሁኔታ ብዙም እንዳልሆነም ተናግሯል።

አብዛኛዎቹ ካባ ማሠራት የሚፈልጉ ሰዎች በማሽን የሚሠራ እንጂ በሰዎች እጅ የሚጠለፍ እንደማይመስላቸው ጠቅሶ፣ በቶሎ እንዲደርስላቸው እንደሚፈልጉም ዓለምሰገድ ይገልጻል፤ ሥራው ጊዜ የሚወስድና ጥንቃቄ የሚፈልግ መሆኑንም ይናገራል። ለተለያዩ ፕሮግራሞች ካባ ሲሠራ ጊዜ የመውሰዱን ያህል ሲለበስም እንዲሁ ጥንቃቄን እንደሚፈልግ ነው የተናገረው።

ዓለም ሰገድ እንደሚለው፤ ለካባ የሚደረገው ጥንቃቄ ከአቀማመጥ ይጀምራል። ሙካሹ የሽቦ ባሕሪ ያለው በመሆኑ በጊዜ ሂደት እንዳይደበዝዝ አየር ማግኘት ይኖርበታል፤ እንደ ሽቶ ያሉ ነገሮች ባይደረጉበት ይመረጣል። ማጽዳት ከተፈለገም ተሠርቶ በተጠናቀቀበት ወቅት ወጥ ሆኖ እንዲቆይ ማድረቂያ የሚቀባ ሲሆን፣ ውሃ ከነካው ስለሚለቅ ውበቱ ይቀንሰዋል። በመሆኑም ማፅዳት በተፈለገበት ወቅት የእጥበት አገልግሎት በሚሰጡ ባለሙያዎች ደረቅ እጥበት ይደረግለታል ።

ዓለምሰገድ ካባን ለመሥራት እንደ ግብዓት የሚያገለገለውን ከፋይ ጨርቅ በሜትር፤ ሙካሽ ደግሞ በኪሎ ገዝቶ ይሠራል። ‹‹የካባ ሥራን የሚያስውበው ሙካሽ ሲሆን፣ ዋጋው እንደምንጠቀመው የሙካሽ ብዛት ይወሰናል›› የሚለው ዓለምሰገድ፤ ካባው ተሠርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ ለገበያ የሚቀርብበት ዋጋ እንደ ሠሪው እንደሚወሰን ይናገራል። አንድ ባለሙያም ካባው ላይ የሚጠቀመውን ሙካሽ ሳይሰስት ጥንቅቅ አድርጎ የሠራው እንደሆነ ዋጋው ከፍ ያለ እንደሚሆንም ጠቅሶ፤ ተጨማሪ ግብዓቶቹን የሚገዛበት ዋጋ ካባው በሚሸጥበት ዋጋ ላይ ለውጥ እንደሚያመጣም አመላክቷል ።

ከዚህ ቀደም አንድ ሜትር የከፋይ ጨርቅ ከ50 እስከ 80 ብር፣ ሙካሽ ደግሞ ከአንድ ኪሎ እስከ አንድ ኪሎ ከግማሽ ሙካሽ የሚፈጅ ሲሆን አንዱ ኪሎ በ80 ብር ይሸጥ ነበር። ካባው ተሠርቶ ሲሸጥም ሁለት ሺ ብር ያወጣ ነበር። አሁን ላይ ግን አንድ ሜትር ከፋይ ጨርቅ አንድ ሺ ብር፣ አንድ ኪሎ ሙካሽ ደግሞ አምስት ሺህ ብር ለገበያ የቀረበበት ዋጋ ነው። ታዲያም ጥራት ያለው ጥንድ ካባ 20 ሺህ ብር እና ከዛም በላይ ለገበያ ይቀርባል። ለገበያ በሚቀርብበት ጊዜም ለሚፈልጉት ሁነት የሚገዙም፣ ተከራይተው የሚጠቀሙም አሉ ሲል ዓለምሰገድ አስታውቋል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ተሠርተው ካሳለቁ ፈርሰው ቢያልቁ!

**ዋለልኝ አየለ**

አንዳንድ ሙያዊ ነገሮች ለተራው ዜጋ ግልጽ አይሆኑም። ከእነዚህ ሙያዊ ነገሮች በተደጋጋሚ ጥያቄ የሚፈጥርብኝ የመንገዶች ግንባታ ነገር ነው። አንዳንድ መንገዶች ሲፈርሱ ሳይ በተሻለ ጥራት በአዲስ መልክ ሊሠሩ ነው ብዬ አስባለሁ። ከዛሬ ነገ የሚያልቁበትን ጊዜ እየጠበቅኩ የተቆፋፈሩ መንገዶችን በተስፋ አልፋለሁ። ምክንያቱም በታዳጊ ሀገር ውስጥ የተሻለ ነገር ለማግኘት የግድ ዋጋ መከፈል አለበት።

እዚህ ላይ ታዲያ በተደጋጋሚ የምታዘበው ነገር ተሠርተው አለማለቃቸውን ሳይሆን ፈርሰው አለማለቃቸውን ነው። የመጀመሪያው ዙር ማፍረስ የሥራው ባሕሪ ነው ብዬ አልፈዋለሁ። ከዚያ የሆነ ነገር ሲነጠፍበት ወይም ሲለብስ አየዋለሁ። ከቀናት ወይም ሳምንታት በኋላ ደግሞ ያ የተነጠፈው ወይም የለበሰው ነገር ሲፈርስ ይታያል። እንደገና ይቆፈራል። አሁንም ሌላ ጊዜ የተቆፈረው ነገር የሆነ ነገር ይሠራበታል። በቃ ተሠርቶ ሊያልቅ ነው ሲባል እንደገና ደግሞ ይፈርሳል። በዚህ የመሥራትና የማፍረስ መፈራረቅ ውስጥ መንገደኛ እየተጉላላ ነው። ይሄኔ ነው እንግዲህ ተሠርቶ ማለቁ ባይሳካ እንኳን ፈርሶ ማለቁን የምንመኘው። ምክንያቱም ቢያንስ በአቧራው ላይ እንኳን ለመሄድ ፈርሶ ማለቅ አለበት።

እንደዚያ የሚያደርጉበት ምክንያት ይኖራቸው ይሆናል። ምናልባትም በተደጋጋሚ የዲዛይን ስህተት እያጋጠማቸው ይሆናል። ወይም መሠራት በሌለበት መንገድ ስለተሠራ እንደገና አፍርሱት እየተባሉ ይሆናል። ይህን ሁሉ ግን ተራው ዜጋ ሊያውቀው አይችልም። ነዋሪው ለረጅም ጊዜ መጉላላቱን ብቻ ነው የሚያስብ። ስለዚህ እንዲህ አይነት የመንገድ ሥራዎች ሲሠሩ በቂ ጥናት ተደርጎ፣ መጀመሪያ ዲዛይኑ አልቆ፣ በቂ ክትትል እየተደረገበት መሆን አለበት።

አንዳንድ ጊዜ ደግሞ እንዲህ ይሆናል። ማፍረሱም ሆነ መሥራቱ ይቆምና በፈረሰበት ወይም ሥራው በተጀመረበት ይቆማል። እነዚያ አካፋና ዶማ ይዘው የሚታዩ ሠራተኞች፣ እነዚያ የሚቆፍሩ ተሽከርካሪ ማሽኖች ልክ ሥራ እንደጨረሱ ሁሉ ይጠፋሉ። ‹‹በቃ በዚሁ ሊቀር ነው!›› እያልን ስንጨናነቅ ከሳምንታት ወይም ወራት በኋላ ደግሞ ብቅ ይላሉ። በዚህ ሁሉ ክፍተት ውስጥ መንገደኛው እየተጉላላ፣ በተለይም አካል ጉዳተኞች እየተቸገሩ ነው።

እርግጥ ነው ሀገራችን ድሃ ናት። ነገሮች በታሰበው ልክ አይሄዱም። መንግሥትም ቢሆን በታሰበው ልክ ቢሄድለት አይጠላም። ሥራዎች የሚጓተቱት በሀገሪቱ የዕድገት ደረጃ ሁኔታ መሆኑ ይታወቃል። ሆኖም ግን የክትትል ችግርም አለ። ለምሳሌ አንድ ሥራ ተቋራጭ የሆነ መንገድ ሲጀምር በተከተታይ ጊዜ ሊሠራ መሆን አለበት። በታሰበው የጊዜ ገደብ ውስጥ ሊጨርስ መሆን አለበት። በተባለው ጊዜ ውስጥ ካልጨረሰ ወይም በመሐል ሥራውን የሚያቋርጥ ከሆነ መጠየቅ ሊለመድ ይገባል።

የአሁኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሚመሰገንባቸው ነገሮች አንዱ የጀመረውን ፕሮጀክት በፍጥነት መጨረስ ነው፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ከታሰበው ጊዜ ቀድሞ በመጨረስም ነው። ከፕሮጀክቶች ሁሉ ግን የመንገድ ጥገናዎች ላይ አሁንም የመጓተት ችግር አለ። ለምሳሌ፤ እንደ ላምበረት ያሉ አገር አቋራጭ መናኸሪያዎች አካባቢ ያሉ መንገዶች አሁንም እንደፈራረሱ ናቸው። አንድ ክረምት ጨርሰው እነሆ አሁንም ሌላ የዝናብ ጊዜ ሊመጣ ነው። የተቆፈረው አቧራ በተሽከርካሪዎች ጎማ ሲነካ አካባቢውን አቧራ በአቧራ ያደርገዋል። ይህ ከሚሆን ሥራው የሚጀመርበት ጊዜ ሳይወሰን ማፍረሱ ባይቀድም ጥሩ ነበር።

አራት ኪሎ ከትምህርት ሚኒስቴር እስከ አራዳ ክፍለ ከተማ ድረስ ያለው የእግረኛ መንገድ መፍረስ ከጀመረ ቆይቷል። እስከ አሁን ግን በተደጋጋሚ ሲሠራና ሲፈርስ እንጂ ሲያልቅ አይታይም። ይቆፈራል፤ የሆነ ነገር ይደረግበታል፤ ከዚያ እንደገና ይቆፈራል። በመሐል ደግሞ ማፍረሱም መሥራቱም ይቆማል። እንዲህ እንዲህ እያለ የዝናብ ጊዜ ከመጣ አሁንም አስቸጋሪ ሆኖ ይቆያል ማለት ነው።

ይህ እንግዲህ የግንባታ ሂደት ስለሆነ መጓተት ነው ብለን እንለፈው፤ ቢያንስ የሆነ ጊዜ ያልቃል። ከዚህም በላይ ችግር የሚሆነው ግን አንዱ አካል ሠርቶ ሲሄድ ሌላው አካል አፍርሶ የሚተወው ነገር ነው። ይህ ለብዙ ዓመታት የቆየንበት መጥፎ ልማድ ነው። መንገድ ሠሪው አካል ሠርቶ ይሄዳል። ሌላው አካል ደግሞ የሚቀብረው ወይም የሚያነጥፈው ይኖረኛል በሚል አፍርሶ ይቀብራል። ለመዘርጋት የተቆፈረው ጉድጓድ ግን እንደ ነገሩ ለበስ ለበስ ተደርጎ ይተዋል። የእሱ ሥራ የተፈለገውን ነገር መዘርጋት ብቻ ነው። ለመዘርጋት አስፋልቱ ሲቆፈር የሚወጣው አፈር ግን ከዳርና ከዳር ተቆልሎ ይቀራል። ያ አፈር በበጋ አቧራው፣ በክረምት ጭቃው የአካባቢውን ገጽታ ያበላሻል።

ሌላው የምንታዘበው ደግሞ የጥራት ችግር ነው። ለምሳሌ ‹‹ቴራዞን›› የሚባለው የእግረኛ መንገድ ንጣፍ በብዙ ቦታዎች ላይ ሲያስቸግር ይታያል። የተነጠፈው ንጣፍ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ መነሳት ይጀምራል። ይህ ሲሆን በተለይም በዝናብ ወቅት በውስጡ ውሃ ይይዛል። በውስጡ የተጠራቀመው ውሃ ንጣፉን ከአንደኛው ጫፍ ሲረግጡት ውሃው ወደ ላይ ይረጫል። ይሄኔ በልብስ ላይ ወይም በሰውነት ላይ ያርፋል ማለት ነው። ስለለዚህ ብዙ ሰው እየተሳቀቀ ነው የሚረግጠው፤ ወይም ላለመንካት ዳር ዳር ሲል ከተሽከርካሪ ጋር ሊጋጭ ይችላል።

በዚሁ እግረ መንገድ ግን አንድ ትዝብት እንጨምር። አንዳንድ ቦታዎች ላይ የእግረኛ መንገዶች በተሽከርካሪ ይያዛሉ። ለምሳሌ፤ መገናኛ እስራኤል ኤምባሲ አካባቢ ያለው የታችኛው የእግረኛ መንገድ በተሽከርካሪዎች የተያዘ ነው። ሰዎች የሚሄዱት በዋናው አስፋልት ላይ ከተሽከርካሪ ጋር እየተጋፉ ነው። ይህ ደግሞ ለአደጋ ያጋልጣል ማለት ነው።

አንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ የእግረኛ መንገዱ በግንባታ ምክንያት ይታጠራል። ይህ ሲሆን እግረኛ በዋናው አስፋልት ጥግ ጥግ በኩል ያልፋል። እዚህ ላይ ታዲያ የሚያጋጥመው ችግር ብዙ አሽከርካሪዎች የእግረኛ መሄጃው ላይ ተሽከርካሪ አቁመው ይጠፋሉ። ለምሳሌ፤ ከአራት ኪሎ ወደ ፒያሳ በሚወስደው መንገድ ራስ መኮንን ድልድይ አካባቢ ያለውን ልብ በሉ። እግረኛ የሚሄደው ከተሽከርካሪ ጋር እየተደበላለቀ ነው። የእግረኛ ማለፊያዋን ከጫፍ እስከ ጫፍ ተሽከርካሪ ይቆምበታል። ባለቤቶች በውስጡ አይታዩም። እነዚህ ባለመኪኖች ግን ቢያንስ ለንብረታቸው ደህንነት አይሰጉም?

በእንዲህ አይነት ድርጊቶች ላይ ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል። በበዓል ወይም የሚመረቅ ነገር ሲኖር መንገድ ሲዘጋ ብቻ ነው ‹‹ለአጭር ጊዜም ሆነ ለረጅም ጊዜ ተሽከርካሪ ማቆም የተከለከለ ነው›› የሚል ክልከላ የምንሰማው። ተሽከርካሪ መቆም የሌለበት ቦታ ላይ መቼውንም ቢሆን ሊቆም አይገባም። በተለይም የእግረኛ መንገድ ዘግቶ መቆም ሊከለከል ይገባል።

# በውጭ የሚኖረው ሁለተኛው ትውልድ ወደ አባቶቹ ሀገር መምጣቱ ትሩፋቱ ብዙ ነው

**እስማኤል አረቦ**

ሀገር የምትገነባው በትውልዶች ቅብብሎሽ ነው። አንዱ ትውልድ ካለፈው ትውልድ የተረከበውን በማሳደግ የራሱን ዕሴቶች እየጨመረ አሻራውን እያሳረፈ ይሄዳል። ኢትዮጵያ በዚህ መልኩ ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ እየተሸጋገረችና ሉዓላዊነቷንና አንድነቷን እያስጠበቀች ዛሬ ላይ ደርሳለች።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ የትላንት ተከታታይ ትውልዶች ውጤት ነች። ኢትዮጵያ በአርሶ አደሩና ትምህርት ቀመስ በሆኑ ዜጎቿ እየተሠራችና እየተበጀች ዘመናትን የተሻገረች ሀገር ነች። በቀደሙት ዘመናትም የድንበር ተሻጋሪ ገናና ታሪክ ባለቤትም ነች።

እነዚህ ታሪኮች በፈጠሩት መነሳሳት በየዘመናቱ የነበሩ መንግሥታትም ይህንኑ እውን ለማድረግ የራሳቸውን መንገድ ሲከተሉ ቆይተዋል። ዘመናዊ ሥልጣኔ እንደሀገር ከተዋወቀበት ከአጼ ምኒሊክ ዘመነ መንግሥት ጀምሮ ሳይንስና ቴክኖሎጂን ከአደጉት ሀገራት ቀስመው ወደ ሀገር ለማምጣት በርካታ ዜጎች ለትምህርት ወደ አውሮፓና አሜሪካ አቅንተዋል።

አብዛኞቹ ከአውሮፓና አሜሪካ ያገኙትን ዕውቀት ወደ ሀገር ተመልሰው በተግባር ለመተርጎም ሲሞክሩ አንዳንዶቹ ደግሞ ኑሯቸውን በእነዚሁ ሀገራት አድርገዋል። ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ “pioneers of Ethiopia” በሚለው መጽሐፋቸው በአፄ ምኒሊክና በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ መንግሥት ወደ ውጭ ሀገራት ለትምህርት ከተላኩት ኢትዮጵያውያን ውስጥ አብዛኞቹ ወደ ሀገራቸው ተመልሰው በቀሰሙት ዕውቀት ሀገራቸውን ለማገልገል ሞክረዋል።

የደርግ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ግን በሀገር ውስጥ በነበረው የፖለቲካ ሽኩቻና በኢኮኖሚ ችግር ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያውያን ኑሯቸውን በአውሮፓና አሜሪካ ለማድረግ ተሰደዋል። እነዚህ ኢትዮጵያውያን በሚኖሩባቸው ሀገራት ትዳር መሥርተው ቤተሰብ አፍርተዋል። ልጆች ወልደዋል።

ከእነዚህ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን የተወለዱት ልጆች /ሁለተኛዎቹ ትውልዶች/ አብዛኞቹ ኢትዮጵያን በምናብ እንጂ በአካል አያውቋትም። የማንነታቸው መሠረት የሆነችውን የአባቶቻቸውን ሀገር ከወላጆቻቸው ከሚሰሙት ቁንጽል ታሪክ ውጪ በገቢር መጥተው አላዩዋትም። ይህ እውነትም ስለሀገራቸው በልበ ሙሉነት ለመናገር የሚያስደፍራቸው አይደለም።

ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ የተባሉ ምሁር ‹‹ኢትዮጵያውያን በአሜሪካ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ ትንተና›› በሚል ባዘጋጁት መጽሐፍና እና ስለሁለተኛው ትውልድ ባወሱበት ምዕራፍ እንዳብራሩት “ የአዲሱ ትውልድ አባላት በትውልድ ኢትዮጵያዊ በመሆናቸው በባሕላቸው፤ በአስተዳደጋቸው፤ በአመለካከታቸው፤ በኑሯቸው ኢትዮጵያዊ እንዲሆኑ እንጠብቃለን” ብለዋል።

በሌላም በኩል አሜሪካ ውስጥ ተወልደው ስላደጉ አሜሪካዊ ባህል፤ አሜሪካዊ አኗኗር፤ አሜሪካዊ አስተሳሰብ፤ አሜሪካዊ አመለካከት ሊኖራቸው ይችላል። እነዚህ ወጣቶች ግን ማን ናቸው? የሚል ጥያቄ አንስተዋል። በርግጥም ትልቁ ጥያቄ ይህ ነው። በእነዚህ ወጣቶችም ዘንድ ዘወትር የሚመላለሰው ጥያቄ ማንነታቸው የተሳሰረው የዘር ሐረጋቸው ከተቋጠረባት ከኢትዮጵያ ጋር ወይስ ተወልደው ካደጉባት ከአሜሪካ ጋር? ይህ በአግባቡ መልስ የሚያሻው ጥያቄ ነው።

ማንነትን መረዳት፤ በሕይወት ረጅም ጉዞ ውስጥ ለብዙ ጥያቄዎች ምላሽ የሚሰጥ ጥልቅ ሰብዓዊ ጉዳይ ነው። ለጥቁር አሜሪካውያን እስካሁን ያልተመለሰ ጥያቄና ለሥነልቦናም ቀውስ እየዳረጋቸው ያለው ይኸው የማንነት ጥያቄ አለመመለስ እንደሆነም ብዙ ትናንቶች በስፋት የሚያስገነዝቡት ነው ።

> **እነዚህ ኢትዮጵያውያን የማንነታቸው መሠረት የሆነው ኢትዮጵያዊነትን በሁለንተናዊ መገለጫው ማወቅ አለባቸው። እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ቢናገሩም፤ ባሕሪና አኗኗራቸው አሜሪካዊ ቢሆንም ማንነታቸው ግን ኢትዮጵያዊነት ነው። ይህንን ማንም ሊቀይረው የማይችለው እውነት ነው**

በተለይም የእነዚህ ኅብረተሰብ ክፍሎች ዝርያዎች ወደ አሜሪካ ከመጡ ዘመናትን ያስቆጠሩ ከመሆናቸውም በሻገር በአግባቡም ሀገራቸውንና ማንነታቸውን እንዲያውቁ አለመደረጋቸው ሁልጊዜ ከራሳቸው ጋር እንዲሟገቱ አድርጓቸዋል። ኢትዮጵያውያንም ይህ ችግር እንዳይገጥማቸው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ታደሰ ወልደ ጊዮርጊስ ከላይ ባነሳነው መጽሐፋቸው እንዳወሱትም፤ ለአሜሪካ ሕዝብ ዋነኛው ጉዳይ ዜግነት ሳይሆን ባሕልና ማንነት ነው። አሜሪካ የተወለዱ እና ያደጉ ኢትዮጵያውያን ሕጋዊ ዜግነታቸው አሜሪካዊ ቢሆንም የሚታየው ባሕልና ማንነታቸው በመሆኑ ከኢትዮጵያዊ ውጭ በሌላ ሊታወቁ አይችሉም። በውጭ ዓለም መወለድና ማደግ ማንነትን እንደማይቀይርም አጠንክረው አመልክተዋል ።

ለነዚህ ኢትዮጵያውያን የማንነታቸው መሠረት የሆነው ኢትዮጵያዊነትን በሁለንተናዊ መገለጫው ማወቅ አለባቸው። እንግሊዝኛ አቀላጥፈው ቢናገሩም፤ ባሕሪና አኗኗራቸው አሜሪካዊ ቢሆንም ማንነታቸው ግን ኢትዮጵያዊነት ነው። ይህንን ማንም ሊቀይረው የማይችለው እውነት ነው።

ከዚህ የተነሳ በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሁለተኛ ትውልዶች ማንነታቸውን በአግባቡና በትክክል አውቀው እንዲያድጉ መደረግ ተገቢ ነው። ማንነታቸው ኢትዮጵያዊ፤ ሀገራቸው ደግሞ ኢትዮጵያ መሆኗን በተጨባጭ ማወቅ ይኖርባቸዋል። ይህንን ማወቁ ድንገትም ለነገ ሕይወታቸው ስኬት ተጨማሪ አቅም ሊሆን ይችላል ።

ይህ ትውልድ ሀገሩ የሰው ዘር መገኛ፤ የብዙ ሥልጣኔዎች ባለቤት መሆኑዋን ሊያውቅ፤ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከአርባ ጊዜ በላይ ስሟ የተወሳ፤ በቁርዓን እና በሐዲስ ውስጥ ስሟ የተከበረ ድንቅ ሀገር መሆኑዋን ሊረዳ ይገባል። ከዚህም በላይ በማንነቱ እንዲኮራ የሚያስችሉት በርካታ ስጦታዎች ባለቤት እንደሆነች ሊያውቅ ያስፈልጋል።

ይህንኑ ተጨባጭ እውነታ ታሳቢ በማድረግ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ሁለተኛ ትውልድ ኢትዮጵያውያን ወደ ሀገራቸው መጥተው ታሪካቸውን፤ ወግና ባሕላቸውን እንዲያውቁ መንግሥት ያቀረበው ጥሪ በሁሉም መልኩ የሚደገፍና የሚበረታታ ነው። ይህንኑ ጥሪ ተቀብለው እየመጡት ላሉትም የአየር ትኬትና የሆቴል መስተንግዶ ቅናሽ ከማድረግ ጀምሮ የተለያዩ ማበረታቻዎች መደረጉም እውቅና ሊሰጠው የሚገባ ነው።

በመንግሥት የተደረገውን ጥሪ ተከትሎም ከታኅሣሥ 20 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ መስከረም ወር 2017 ዓ.ም መጨረሻ ቀናት በሦስት ዙሮች በርካታ ቁጥር ያላቸው የትውልዱ አባላት ወደ ኢትዮጵያ ይመጣሉ ተብሎ ይታሰባል። ወደ ሀገር ውስጥ መምጣታቸው በርካታ ትሩፋቶችን ይዞም እንደሚመጣ ይጠበቃል ።

ጥሪው በዋነኝነት ትውልዱ ሀገሩን እንዲያውቅ ዕድል ይሰጠዋል። ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መገኛ፤ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ብቸኛዋ ሀገር እና የጥቁር ሕዝቦች ኩራት፤ በተፈጥሮ ሃብት የታደለች፤ በዩኔስኮ 16 ቅርሶችን ያስመዘገበች ብቸኛዋ አፍሪካዊት ሀገር፤ የአፍሪካ ዋንጫ መሥራች፤ በኮርያ፤ በኮንጎ እና በሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሰላም በማስከበር አንቱታን ያተረፈች ሀገር የመሆኑን እውነታ ያውቃል።

የአባቶቹ ሀገር /ሀገሩ/ በዓለም ውስጥ የራሳቸው ፊደል ካላቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ፤ በአፍሪካ ደግሞ ብቸኛዋ ሀገር እንደሆነች በዚህም ከራሷ አልፋ ለአፍሪካውያን ኩራት ጭምር የሆነች ሀገር እንደሆነች ለማወቅ የተመቻቸ ዕድል ይፈጠርለታል።

ኢትዮጵያ ጥንታዊ የሰው ልጅ መገኛ ከመሆኗም ባሻገር የራሷን ማንነትና ታሪክ አስጠብቃ የቆየች የጥቁር ሕዝቦች መመኪያ መሆኗን፣ ይህ ታሪክ ደግሞ ሀገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን በውጪ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን /የሁለተኛውን ትውልድ/ መኩሪያ ታሪክ ጭምር ነው። ይህን ማወቅ በራሱ/በማንነቱ ያለውን ኩራት ከፍ የሚያደርግ ነው።

ትውልድ በማኅበራዊም ሆነ በሥነ ልቦና ረገድ ጠንካራ ማንነት ሊገነባ የሚችለው ታሪኩን፤ ባሕልና ወጉን መረዳት ሲችል ነው። ከኢትዮጵያ ይዞት የሄደው ባሕልና ማኅበራዊ ሕይወት ስለሌለው እና ሙሉ ለሙሉ በውጭ ባሕል ያደገ በመሆኑ እንደ ቀደመው ትውልድ ጠንካራ ስብዕና አይኖረውም። ጥሪውን ተከትሎ ሲመጣ የሀገሩን ታሪክ፤ ወግና ባሕል እንዲሁም ማኅበራዊ ሕይወት በቀላሉ በመረዳት በራሱና በሀገሩ ይኮራል።

ከወላጆቻቸው ሀገር ጋር ቁርኝት እንዲፈጥሩ፣ መነሻ ሀገራቸውን በአግባቡ እንዲረዱና በማንነታቸው እንዲኮሩ ያስችላል። ከዚህም ባለፈ ከሀገራቸው ጋር ቋሚ ግንኙነት እንዲፈጥሩ እና መነሻቸውንም እንዲያውቁ ይረዳቸዋል። በአባት አያቶቻቸው ታሪክ እንዲኮሩ ዕድል ይፈጥርላቸዋል።

ይህ አጋጣሚ አባቶቻቸውና አያቶቻቸው ያቀኗትን ሀገር እንዲያውቁና የትውልድ ቅብብሎሽ እንዲኖር ያደርጋል። የወላጆቻቸው ሀገር ክብርና ዝና በአካል ተገኝተው እንዲረዱ ያስችላል። ኢትዮጵያ በትውልድ ቅብብሎሽ የጸናች ሀገር ነች። የትላንቱ ትውልድ በከፈለው መስዋዕትነት የጥቁር ሕዝቦች የነፃነት አክሊል ሆና ዘለቀች ሀገር ነች። ይህችን ድንቅ ሀገር በአካል ተገኝቶ ማየትና መረዳት ከዕድልም በላይ ነው።

ከዚህም በተጨማሪ ሀገራቸው ላይ ዕውቀታቸውንና ገንዘባቸውን እንዲያፈሱ ዕድል ይሰጣል። አዲሱ ትውልድ በሠለጠኑት ዓለማት ያገኘውን የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት ወደ ሀገሩ በማምጣት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚታዩትን ችግሮች ደረጃ በደረጃ ለመፍታት ዕድል ይሰጠዋል።

የኢትዮጵያም ሆነ የሦስተኛው ዓለም አጠቃላይ የኑሮ ደረጃ ከአሜሪካና ከምዕራባውያን የኑሮ ደረጃ ጋር ሲነጻጸር ሰፊ ልዩነት ያለው በመሆኑ ልዩነቱ እስኪጠብ ድረስ አሁንም ፍልሰት ሊቆም አይችልም። ኢትዮጵያውያንም ሀገራቸውን በልባቸው ውስጥ አድርገው የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ምዕራቡ ዓለም በስፋት ሲሰደዱ ቆይተዋል። ከአፄ ኃይለሥላሴ አስተዳደር መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ እስዛሬ ድረስ ፍልሰቱ አልቆመም።

ሆኖም ዋናው ጉዳይ ወደ ውጭው ዓለማት የፈለሱት ዜጎችም ሆኑ እዛው የተወለዱት የሁለተኛው ትውልድ አባላት ለሀገራቸው ምን አበረከቱ? የሚለው ነው። የሚሰደደው ዜጋም ሆነ እዛው የተወለደው ሁለተኛ ትውልድ ዋነኛ ትኩረቱ የምዕራባውያን የአኗኗር ስልት እየተከተሉ በዛው ሰምጦ መቅረት ሳይሆን የኢትዮጵያን ሕዝብ ዘላቂ ችግሮች ለማሻሻል መሞከር ሊሆን ይገባል።

በተለይም በውጭ የሚኖረው ሁለተኛ ትውልድ የተሻለ ትምህርት የቀሰመ፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕውቀት የተራመደ፤ በመጠኑም ቢሆን ጥሪት የቋጠረ በመሆኑ ያሉትን የዕውቀትና የመዋዕለ ንዋይ ሃብቶች ይዞ ወደ ሀገሩ በመምጣት የበኩሉን አሻራ ማሳረፍ ይችላል።

ሁለተኛው ትውልድ ሀገሩን የማወቅ ዕድል ማግኘቱ ትልቅ እድል ከመሆኑም ባሻገር ለኢትዮጵያም ትልቅ ትልቅ ተስፋ ነው። አዲሱ ትውልድ ትምህርት ለማስፋፋት፤ መንገዶችን ለመሥራት፤ መንገዶችን ተደራሽ ለማድረግ፤ ኢንቨስትመንትን ለማሳደግ በአጠቃላይ የተጀመረውን ልማት ወደ ተሻለ ደረጃ ለማድረስ የማይተካ ሚና ይጫወታል።

ዛሬ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ትልቁ የሆነውን የዓባይ ግድብ ገንብታ በማጠናቀቅ ላይ ትገኛለች። ለ33 ዓመታት ተዘግቶባት የነበረውን የባሕር በር ለማስከፈት ከሶማሌ ላንድ ጋር የመግባቢያ ሰነድ ተፈራርማለች። የቱሪስቶችን ቀልብ የሚስቡ በርካታ ተፈጥሮ ሃብቶችን በማልማት ላይ ትገኛለች።

እነዚህና መሰል ተግባራት ደግሞ ወደ ላቀ ደረጃ እንዲሸጋገሩና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሕይወት እንዲለውጡ በሀገር ውስጥ ካለው አቅም በተጨማሪ በውጭ የሚኖረውን ዲያስፖራ በተለይም ደግሞ የሁለተኛውን ትውልድ እውቀትና መዋዕለ ንዋይ ትፈልጋለች።

ይህ ዕድል ደግሞ የኢትዮጵያን ብልጽግና ከማፋጠኑም ባሻገር ሁለተኛውን ትውልድ ከሀገሩ ጋር ቋሚ የሆነ የሥነ ልቦናና የማኅበራዊ ትስስር እንዲኖረው ያደርገዋል።

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ኤፍ-16 ተዋጊ የጦር ጀት ለቱርክ እንዲሸጥ ፈቀደች

በጋዜጣው ሪፖርተር

የአሜሪካ መንግሥት 23 ቢሊዮን ዶላር የሚያስወጡ 40 ኤፍ-16 ተዋጊ ጀቶች ለቱርክ በሽያጭ እንዲተላለፉ ፈቀደ።

ቱርክ ተዋጊ ጄቶቹን እንድትገዛ ፍቃድ የተሰጣት ስዊድን የሰሜን አትላንቲክ የጦር ቃል ኪዳን ድርጅት (ኔቶ) የአባልነት ጥያቄን ከፈቀደች በኋላ ነው።

ቱርክ አዲስ ከምትገዛው 40 ኤፍ-16 ጀቶች በተጨማሪ አሁን በይዞታዋ ላሏት 79 ጀቶች ማሻሻያ ቁሳቁስም ትረከባለች።

ከዚህ በተጨማሪ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ 40 ኤፍ-35 የጦር ጀቶችን ለግሪክ ለመሸጥ ከውሳኔ ስለመድረሱ ለኮንግረሱ አስታውቋል። ግሪክ ለኤፍ-35 ጦር ጀቶች 8.6 ቢሊዮን ዶላር ትከፍላለች።

ስዊድን እአአ በ2022 ሩሲያ ዩክሬንን ከወረረች በኋላ ኔቶን ለመቀላቀል ጥያቄ ማቅረቧ ይታወሳል።

ስዊድን ለኩርድ ተገንጣዮች ድጋፍ ትሰጣለች በሚል ቱርክ ኅብረቱን የመቀላቀል ጥያቄዋን አዘግይታው ቆይታለች።



ቱርክ የጦር ጀቶቹን ለመግዛት ጥያቄ አቅርባ የነበረው እአአ 2021 ቢሆንም ለስዊድን ጥያቄ አዎንታዊ መልስ ሳትሰጥ በመቆየቷ የጦር ጀቶቹ ሽያጭም ዘግይቶ ቆይቷል።

ይሁን እንጂ ከጥቂት ቀናት በፊት ስዊድን ኔቶን ለመቀላቀል ያቀረበችው ጥያቄ በቱርክ ፓርላማ አባላት ድጋፍ አግኝቶ የቱርኩ ፕሬዚዳንት ረሲፕ ታይፕ ኤርዶሃንም ውሳኔውን በፊርማቸው አረጋግጠዋል።

ከዚህ በኋላ ፕሬዚዳንት ጆ ባይደን የኤፍ-16 ጀቶች ሽያጭ መዘግየት እንዳያጋጥመው አሳስበው ነበር።

ሩሲያ በዩክሬን ላይ መጠነ ሰፊ ወረራ መፈጸሟ ቱርክን በጥቁር ባሕር አካባቢ የምትገኝ ወሳኝ የኔቶ አባል ሀገር አድርጓታል።

የጦር መሣሪያ ዝውውር ፍቃድን ከሚሰጠው አራት አባላት ካሉት የኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ ዴሞክራቱ ሴናተር ቤን ካርዲን «ቱርክ ኤፍ-16 አውሮፕላኖችን ለመግዛት ላቀረበችው ጥያቄ ፍቃድ የሰጠሁት ቱርክ የስዊድን ኔቶ አባልነትን በማጽደቋ ነው» ብለዋል።

«ነገር ግን መዘንጋት የሌለበት፤ በቀላሉ ከዚህ ውሳኔ ላይ አልደረስኩም» ብለዋል።

ዴሞክራቱ ሴናተር ቱርክ የሰብዓዊ መብት አያያዟን ማሻሻል ይኖርባታል ያሉ ሲሆን የሩሲያ መጠነ ሰፊ ወረራንም ለማስቆም አንካራ ሞስኮን ተጠያቂ ማድረግ አለባት ብለዋል።

ስዊድን የኔቶ አባል ለመሆን ላቀረበችው ጥያቄ ምላሽ ያልሰጠች ብቸኛ የኔቶ አባል ሀገር ሃንጋሪ ሆናለች።

ሃንጋሪም እንደ ቱርክ ሁሉ ፍቃዱን እንድትሰጥ የሚያደርጉ ለውጦች እየታዩ ነው።

በቅርቡም የሃንጋሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ቪክቶር ኦርባን ከስዊድን አቻቸው ጋር በቡዳፔስት ለውይይት ተቀጣጥረዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## በወንጀል ተጠርጥሮ ለ50 ዓመታት ሲፈለግ የነበረው ጃፓናዊ ራሱን አጋለጠ

በጋዜጣው ሪፖርተር

ቦምብ በማፈንዳት ተጠርጥሮ ለ50 ዓመታት ገደማ ሲፈለግ የነበረው ተጠርጣሪ ሳይገኝ እንዳልቀረ ጃፓን አስታወቀች።

ሳቶሺ ኪሪሺማ ይባላል። 49 ዓመታት ሙሉ 'ይፈለጋል' የሚል ማስታወቂያ ወጥቶበት ቆይቷል። የፖሊስ ማስታወቂያው ላይ ሳቶሺ ፈገግ ብሎ ይታያል።

በመላው ጃፓን ፖሊስ ጣቢያዎች ይህ ማስታወቂያ ለዓመታት ተለጥፎ ቆይቷል።

ቶኪዮ የሚገኝ ሆስፒታል ውስጥ ያለ ግለሰብ ሳቶሺ እኔ ነኝ ብሏል።

በ1970ዎቹ ቦምብ ያፈነዳው ታጣቂ ቡድን አባል እንደነበረና የሚፈለገው ሰው እሱ እንደሆነም ገልጿል።

ፖሊስ የዘረ መል ምርመራ ተደርጎ ውጤቱ እስከሚመጣ እየጠበቀ ነው።

ግለሰቡ በጽና በካንሰር ታሞ ነው ሆስፒታል የገባው።

ምሥራቅ እስያዊ የሆነውና ፀረ-ጃፓን የሆነው ታጣቂ ቡድን አክራሪ ግራ ዘመም ስብስብ ሲሆን፣ ከ1972 እስከ 1975 ባሉት ዓመታት ብዙ የቦምብ ጥቃቶች በጃፓን መዲና በማድረስ ተጠያቂ ይደረጋል።

በአንደኛው የቦምብ ጥቃት ስምንት ሰዎች ተገድለዋል።

በ1974 በሚስትቡሺ ዋና መሥሪያ ቤት ነበር የደረሰው።

የጃፓን ብሔራዊ ፖሊስ በድረ ገጹ እንዳለው፣ ይህ ግለሰብ «ፈንጂን ለመቆጣጠር» የወጣ ሕግን ጥሷል።

«በተከታታይ ቦምቦች በማፈንዳት በፖሊስ ይፈለጋል» በሚል ነው የተገለጸው።

ግለሰቡ በቤት ውስጥ የተሠራ ቦምብ በመቅበር እንዲሁም እንዲፈነዳ በማድረግ ነበር ሲፈልግ የነበረው።

በዚህ በ1975 በደረሰ የቦምብ ፍንዳታ በቶኪዮ ጊንዛ ግዛት የሚገኝ ሕንፃ በከፊል ጉዳት ደርሶበታል።


ሲፈለግ የነበረው ይህ ግለሰብ ከ49 ዓመታት በኋላ ነው ሳይገኝ አልቀረም የተባለው። አሁን 70 ዓመት ሆኖታል።

ሆስፒታል ሲገባ የተጠቀመው ሌላ ስም ነበር።

አሁን ግን ወደ ሕይወቱ ፍጻሜ አቅራቢያ እውነተኛ ስሙን ለመግለጽ እንደሚፈልግ ለሆስፒታሉ ሠራተኞች ገልጿል።

ሆስፒታሉ እንዳለው ከዚህ በኋላ በሕይወት የሚቆየው ለጥቂት ወራት ነው።

# ስፖርት



## ቱሪዝምና ስፖርት የተሳሰሩበት የወንጪ ደንዲ ሩጫ

ብርሃን ፈይሳ

በተፈጥሮ ሀብት የበለጸገችው ኢትዮጵያ በምቹ የአየር ንብረቷና ማራኪ መልከዓ ምድር አቀማመጧ የተለየች ሀገር ነች። ምቹ የአየር ንብረቷ አትሌቲክስን በመሰሉ ስፖርቶች ውጤታማ እንድትሆንም አስችሏታል። እነዚህን ገፀ በረከቶቿ ዘመኑን እንዲዋጁ በማድረግ የስፖርት ቱሪዝምን ለማሳደግ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ውድድሮች በሀገር ውስጥ እንዲካሄዱ ማድረግ ያስችላል።

በቅርቡ በዘመናዊ መልኩ ተገንብተው ለጎብኚዎች እንዲሁም ለስፖርተኞች ግልጋሎት ላይ ከዋሉ የቱሪዝም መዳረሻዎች መካከል አንዱ የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ነው፡፡

የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም መንፈስን ሀሴት የሚሞላ ከፍተኛ ቦታ ላይ የሚገኝና ነፋሻማ አየር ያለው ከመሆኑ ባለፈ አትሌቶችን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ተገንብቶ በቅርቡ መመረቁ ይታወቃል። ይህን ትልቅ የቱሪዝም እሴት ከስፖርት ቱሪዝም ጋር ለማስተሳሰር በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን፣ በኦሮሚያ ቱሪዝም ቢሮ፣ በኦሮሚያ ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ምዕራብና ደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች አዘጋጅነት ታላቁ የወንጪ 10 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ባለፈው ቅዳሜ ተካሂዷል፡፡

በውድድሩ በወንዶች የሸገር ከተማው አትሌት አዲሱ ነጋሽ አሸናፊ ሲሆን፣ የኢትዮ ኤሌክትሪኩ ሞገስ ጥኡማይ እና የጥሩነሽ ዲባባው አትሌቲክስ ማሰልጠኛ ማዕከል አትሌት ኤሊያስ ጫኔ ተከታትለው በመግባት፤ ከወርቅ እስከ ነሐስ ያሉትን ሜዳሊያዎች አጥልቀዋል። ሦስቱ አትሌቶች እንደየደረጃቸውም የገንዘብ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል።

በሴቶች የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ አትሌቶቹ ጌጤ አለማየሁ እና ኑሪት አህመድ አንደኛና ሦስተኛ ደረጃን በመያዝ የወርቅና የነሐስ ሜዳሊያ አጥልቀዋል፡፡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንኳ አትሌት ፎቴን ተስፋዬ ደግሞ የብር ሜዳሊያ አሸናፊ ሆናለች። ውድድሩን ተከትሎም የመካከለኛ ርቀት አትሌቷ ፎቴን፤ ሩጫው ዳገታማ በሆነ ቦታ በንፋሳማ አየር ታጅቦ የተካሄደ ቢሆንም ለአትሌቶች ተፈላጊ መሆኑን ትገልጻለች፡፡ ለስፖርቱ ምቹ የሆነውን ስፍራ ለመጀመሪያ ጊዜ ከመመልከቷ ባለፈ ፈታኝ በነበረው ሩጫ ሁለተኛ ሆና በማጠናቀቋም መደሰቷን ገልፃለች።



**የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም በቀጣይ በየዓመቱ እንደሚካሄድ ተጠቁሟል፣**

በሰሜኑ የኢትዮጵያ አካባቢ በነበረው ጦርነት ለ3 ዓመት ከስፖርቱ ርቃ የቆየችው አትሌት ፎቴን ወደ ቀደመ ብቃቷ ለመመለስ ጥረት እያደረገች ትገኛለች፡፡ በወንጪ ያደረገችው ልዩ ውድድርም ዝግጅቷን የለካችበት ሆኗል። በተያዘው የውድድር ዓመትም ጠንክራ በመሥራት ከወራት በኋላ በሚካሄደው ኦሊምፒክ ሀገሯን ወክላ ለመሳተፍ ጥረት እያደረገች መሆኑንም ተናግራለች፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ምክትል ፕሬዚዳንት አትሌት ገዛኸኝ አበራ፤ ውድድሩ የተካሄደበት የወንጪ አካባቢ ከፍተኛ ስፍራ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ለአትሌቲክስ ስፖርት ምቹ እንደሆነ ይናገራል። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ይህንን በመሰሉ ከፍተኛ ቦታዎች ልምምድ በመሥራት በውጭ ሀገራት ዝቅተኛ ስፍራዎች በሚደረጉ ውድድሮች ላይ መሳተፋቸው ውጤታማ ያደርጋቸዋልም ይላል፡፡ በመሆኑም ፕሮጀክቱ ለአካባቢው ነዋሪና ለቱሪስቶች ብቻም ሳይሆን አትሌቶችን ጨምሮ ለስፖርተኞች ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን ያስረዳል። የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንን ጨምሮ የክልል ፌዴሬሽኖች ስፍራው ላይ የአትሌቶች ማረፊያ መገንባት ቢቻል ልምምድ በመስራት ስፖርቱንም ቱሪዝሙንም ማሳደግ እንደሚቻል ያለውን እምነት ገልጿል።

የቀድሞው የኦሊምፒክና የዓለም ቻምፒዮና የማራቶን ባለድል ‹‹በውጭ ሀገራት ይህንን በመሰሉ ቦታዎች ስንወዳደር የምንመኛቸው ቦታዎች ኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውን አብዛኛዎቻችን አናውቅም። በመሆኑም እኔን ጨምሮ አብዛኛዎቻችን አትሌቶች የተሰማራነው በሆቴል ሥራ ውስጥ ነው፡፡ ነገር ግን ይህንን የመሰሉ ሥራዎች በማከናወን የሀገራችንን ቱሪዝም ከፍ ከማድረግ ባለፈ አትሌቲክስን የሚያሳድግም ነው›› በማለት አስተያየቱን ሰጥቷል።

በውድድሩ ላይ ተገኝተው ለአትሌቶች ሽልማት ያበረከቱት የኢፌዴሪ የሀገር መከላከያ ሚኒስትርና የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ፕሮጀክት ተቆጣጣሪ ዶክተር አብርሃም በላይ፤ ፕሮጀክቱ ለቱሪዝምና ለስፖርታዊ እንቅስቃሴ ምቹ ሆኖ መገንባቱን ጠቁመዋል፡፡ አካባቢው ለተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ባለው ምቹ ሁኔታ በመጠቀም አትሌቶች ልምምዳቸውን እንዲሠሩም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

በገበታ ለሀገር ፕሮጀክት እየተገነቡ የሚገኙት ሀገራዊ የቱሪዝም መዳረሻዎች ስፖርትን ታሳቢ አድርገው የተገነቡ በመሆኑ ለአካል ብቃት እንቅስቃሴ እንዲሁም ለውድድር ምቹ ናቸው፡፡ ይህ ውድድር የተካሄደበት የወንጪ ደንዲ ኢኮ ቱሪዝም ለጎዳና ሩጫ አመቺ ከሆነው ስፍራ ባለፈ ሁለቱን ሐይቆች የሚያገናኝ የ21 ኪሎ ሜትር (ግማሽ ማራቶን) መም ተሠርቷል፡፡ በስፍራው ከዚህ ቀደም የፈረስ ግልቢያና ጉግስ ውድድር የተካሄደ ሲሆን፤ የሩጫ ውድድሩም በየዓመቱ የሚካሄድ ቀጣይነት ያለው መሆኑ ታውቋል፡፡ በተጨማሪም በቅርቡ የብስክሌት ውድድር ለማዘጋጀት እየተሠራ እንደሚገኝ ለማወቅ ተችሏል።